ረቂቅ

# የኢትዮጵያ የጥራት ፖሊሲ

ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**

1. መግቢያ .......... 4

2. የፖሊሲው ጠቀሜታና አስፈላጊነት .......... 5

3. የፖሊሲው ተልዕኮ፣ራዕይ፣ ግብ፣ ዓላማ እና መርሆዎች .......... 6

3.1 ራዕይ .......... 6

3.2 ተልዕኮ .......... 6

3.3 ግቦች .......... 7

3.4 ዓላማዎች .......... 7

3.4.1 አጠቃላይ ዓላማ .......... 7

3.4.2 ዝርዝር ዓላማዎች .......... 7

3.5 እሴቶች እና መርሆዎች .......... 8

4. የፖሊሲ መግለጫ .......... 10

5. የፖሊሲው ወሰን .......... 11

6. የፖሊሲ ዋና ጉዳዮች .......... 11

6.1 የምርትና አገልግሎት ጥራት ማሳደግ .......... 11

6.2 የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማትን ማጎልበት .......... 12

6.2.1 ደረጃዎች .......... 12

6.2.2 ስነ ልክ .......... 13

6.2.3 አክሪዲቴሽን ........ 14

6.2.4 ተስማሚነት ምዘና ........ 14

6.2.5 የቴክኒክ ደንብ ........ 15

6.2.6 ህጋዊ ሥነ ልክ ........ 16

6.3 ሀገራዊ የጥራት ባህል ግንባታ ........ 17

6.4 ጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች (MSME) ........ 18

6.5 ቅንጅትና ትብብር ........ 18

6.5.1 ቅንጅት እና የፖሊሲ ሁኔታ ........ 19

6.5.2 አለም አቀፍና ቀጣናዊ የጥራት መሰረተ ልማት ........ 19

6.5.3 በብሔራዊ የጥራት ምክር ቤት ........ 19

6.5.4 የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ፎረም ........ 19

6.5.5 የቴክኒክ ደንብ ማስተባበር ........ 20

6.6 ጥራትና ዘላቂ ልማት ........ 20

6.7 ባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ........ 21

6.7.1 ስርአተ-ጾታ እና ወጣቶች ........ 21

6.7.2 አካል ጉዳተኞች ........ 21

7. የፖሊሲ ትግበራ መዋቅር ........ 22

7.1 የሕግ ማዕቀፍ ........ 22

7.2 ተቋማዊ ዝግጅት ....... 23
7.2.1 የጥራት መሠረተ ልማት ተቋማት ....... 23
7.2.2 አጋር አካላት ሚና ....... 26
7.3 የጥራት ፖሊሲው ማስፈፀሚያ ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች ....... 27
7.3.1 ብሄራዊ የጥራት መሰረተ ልማት የፋይናንስ ድጋፍ ....... 30
7.4 የፖሊሲው ክትትልና ምዘና ስርዓት ....... 30
7.4.1 የአመልካች አይነቶች ....... 30
7.4.2 የፖሊሲ ክለሳ ....... 31
8. የፖሊሲው ስርጭት ....... 32
9. ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ ....... 32
10. የቃላት ፍች ....... 32

## 1. መግቢያ

የዘመነ ግሎባላይዜሽን የንግድ ማዕቀፍ ምርትና አገልግሎቶች በአቅርቦት ሰንሰለት ዉስጥ እንዲቆራኙ ምቹ ከባቢን ፈጥሯል፡፡ ኢትዮጵያም በዚህ ዓለም አቀፋዊ የንግድ ትስስር ዕድገት ተጠቃሚ በመሆን በማህበራዊና በኢኮኖሚ ዘርፍ ልማትን ማረጋጋጥ፣ ድህነትን መቀነስና በአካባቢ ላይ የሚደርስ ተጽዕኖን መቋቋም ይኖርባታል፡፡ በዚህም የተነሳ በአሁኑ ወቅት የምርትና አገልግሎት ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ የፖሊሲ አዉጪዎች ትኩረትን በከፍተኛ ሁኔታ በማግኘት ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ አምራቾች፣ላኪዎች ወይም አቅራቢዎች በዚህ አለማቀፋዊ የንግድ ትስስር ሲገቡ የሚያጋጥማቸዉን ፈታኝ ሁኔታ በመረዳት መፍትሄ ማስቀመጥ ተገቢ ነዉ። ለዚህ ምክንያት የሚሆነው በዓለም አቀፉ ገበያ በተለይም በወጪ ምርቶች መዳረሻ አገራት የሚገኘዉ ሸማች በመረጃ የዳበረና ንቃተ ህሊናዉ ከፍ ያለ ከመሆኑም ባሻገር በምርትና አገልግሎቶች ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር የሚያደርጉ ተቋማት ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥጥራቸዉን እያጠበቁ ስለሚገኙ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በአንድ ወገን የወጪ ምርት መዳረሻ ገበያዎች በአቅርቦት ሰንሰለት ዉስጥ ብዛት ያላቸዉን አገራት በማሳተፍ፣ አገልግሎቶችና ግብአቶች ጥራታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ በአነስተኛ ዋጋ፣በተፈላጊ መጠን፣ በአስተማማኝ ሁኔታና በዘላቂነት እንዲቀርቡላቸዉ ይፈልጋሉ።በሌላ በኩል ላኪ ሃገራት ለተመሳሳይ የምርት መዳረሻ ገበያ ተመሳሳይ፣ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ ብሎም የተቆጣጣሪ አካላትን መስፈርት ያሟላ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ግብአት በማቅረብ በሂደቱ ብቸኛ ተጠቃሚ ለመሆን ዉድድሩን አጠናክረዉታል።

በአንጻሩ አብዛኛው የኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎቶች ለብክነትና ብክለት የተጋለጡ፣ ጥራትና ደህንነታቸዉ ያልተጠበቀና ዋጋቸዉም ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ኢንዱስትሪያላይዜሽን በሚደረገዉ መዋቅራዊ ሽግግር ላይ ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በተጨማሪም በስፋት ገበያ ዉስጥ የተሰራጩና ጥቅም ላይ የዋሉ ምርትና አገልግሎቶች የምርት ዱካቸዉ በትክክል የማይታወቅ ወይም በከፍተኛ ሁኔታ የጥራትና ደህንነት ችግር ያለባቸዉ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ለህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ጉልህ የስጋትና አደጋ መንስኤ ከመሆናቸዉም በላይ በአገራዊ ምርትና አገልግሎቶች ተወዳዳሪነት ላይ እንቅፋት መሆናቸዉ እሙን ነዉ፡፡ ስለሆነም አምራቹና አገልግሎት ሰጪዉም ሆነ አቅራቢዉ ቀጣይነቱ የተረጋገጠ፣ ፍላጎት መራሽ፣ ደንበኛ ተኮር፣ ምሉዕ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን በመቋቋም አገልግሎቱን ማስቀጠል የሚችል፤ የመደገፍ፣ የማብቃትና ቁጥጥር ተልዕኮን ያነገበ እና የተሰናሰለ የጥራት መሰረተ ልማት ምህዳር ተግባራዊና ተደራሽ ማድረግ ዋነኛ የፖሊሲ ስልት ነዉ፡፡ ይህ ማዕቀፍ ከተናበበ መዋቅራዊ አሰራርና የቴክኒክ ደንብ አፈፃፀም ጀምሮ፣ የደረጃ ዝግጅትና ትግበራ፣ሥነ ልክ፣ አክሪዲቴሽን፣ ተስማሚነት ምዘና፣ የገበያ ክትትል፣ የአቅም ግንባታ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የተግባቦት፣የስልጠና እና ትምህርት ስራዎችን በማቀናጀት የጥራት ባህል ግንባታ እንዲያካትት ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡

ይህንን ሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታን በቅጡ በመረዳት የኢትዮጵያ መንግስት የጥራት መሰረተ ልማት ስትራቴጂ ቀርፆ ወደ ተግባር የገባ ሲሆን አገልግሎቱን የሚሰጡ አካላት ማለትም የደረጃ፣ ሥነ ልክ፣ አክሪዲቴሽን እና ተስማሚነት ምዘና ተቋማትን ቀዳሚ ትኩረት ሰጥቶ እያጠናከራቸዉ ይገኛል፡፡ከዚህ በተጨማሪም የገቢና ወጪ ምርትን ጨምሮ ክትትሉንና ቁጥጥሩን ለማጠናከር ሴክተር ተኮር ተቆጣጣሪ አካላት በአዲስ መልክ ተጠናክረዉ ከመቋቋማቸዉም በላይ ሴክተሮችን የሚደግፉ የአቅም ግንባታና የምርምር ኢንስቲትዩቶች ከግሉ ሴክተር ጋር ተደጋግፈው ውጤታማ የሚሆኑበት ምህዳር ፈጥሯል፡። ይህ አስቻይ ሁኔታ የተናነበበ እና የተቀናጀ ርብርብ በማድረግ ወደ ዉጤታማነት በመቀየርና አገራዊ ልማቱንና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ አገራዊ ጥረቶችን የሚያስተሳስር የጥራት ፖሊሲ መኖሩ ታምኖበታል፡፡

በዚህም የተነሳ መንግስት የጥራት መሰረተ ልማት ስርዓትን በጥብቅ መሰረት ላይ እንዲቆም ካለው ቁርጠኝነት በመነሳት ይህን የጥራት ፖሊሲ ለመጀመሪያ ጊዜ አውጥቷል፡፡ፖሊሲው አገራዊ የልማት ግቦችን እና አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርሞችን ከግባቸዉ እንዲደርሱ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋና የተሳለጠ የጥራት መሰረተ ልማት ስርአትን በማስፈን በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በአቅም ግንባታ እና በቁጥጥር ላይ የተግባር ድግግሞሽን ያስቀራል፡፡

በአጠቃላይ ተጠያቂና ተገማች አሰራርን በቀጣይነት በማሻሻል ፍትሃዊ የንግድ ዉድድር እንዲሰፍን በማድረግ፣አገራዊ ምርትና ምርታማነትን በአይነት፣በጥራት፣ በመጠን በማሳደግና እሴት በመጨመር የገቢ ምርቶችን መተካት እንዲሁም የወጪ ምርትና አገልግሎት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማስቻል ሀገራዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ይህ የጥራት ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡ የፖሊሲ ሰነዱ በዋናነት የፖሊሲ አስፈላጊነት፣ የፖሊሲ ዓላማዎችን፣ የፖሊሲ ጉዳዮችንና ዝርዝር አቅጣጫዎችን እንዲሁም የፖሊሲ ትግበራ ስልቶችን ይዟል።

## 2. የፖሊሲው ጠቀሜታና አስፈላጊነት

ኢትዮጵያ በ2022 የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት የመሆን ራዕይን ለማሳካት የሚያስችል የ10 አመት የልማት እቅድ አስቀምጣለች ፡፡ ይኸውም በኢንዱስትሪ ፣ በማዕድን ፣ በአይሲቲ ፣ በቱሪዝም እና በግብርና ምርታማነትን በማሳደግ እና እሴት በመጨመር የምርት መዳረሻ ገበያን ማበራከት ታሳቢ ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ያልተጠናከረና የምርቶቹም ጥራት ዝቅተኛ መሆን በኢኮኖሚዉም የሚጠበቅበትን አስተዋፅዖ ማበርከት አልቻለም፡፡ ወጪ ምርቶቻችን የመዳረሻ አገራትን/የተቀባይ አገራትን መስፈርቶች ማሟላት አለመቻላቸዉ ምርቱን ለማስወገድ የሚኖረውን ተጨማሪ ወጪ ጨምሮ አገራዊ ገፅታን በማጠልሸት ዋጋ እያስከፈላት ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ የጥራት መሰረተ ልማት እስከ አሁን ድረስ ስራዎችን በሚገባ ለማከናወን የሚያስችል ተገቢ አቅም በመገንባት ላይ ሲሆኑ ከተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ለተገልጋዮቻቸው የሚሰጡት አገልግሎት ውጤታማ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተቆጣጣሪ አካላት ተግባራት ለጥቅም ግጭት የተጋለጡ መሆንና የሃላፊነት መደበላለቅ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ጥራትና ደህንነቱ ያልተረጋገጠ ምርትና አገልግሎት ይዞ ወደ ገበያ ለመግባት የሚፈልገዉን አመለካከቱ የተዛነፈ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ላይ ተገቢዉን ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ በመዉሰድ ዉድድሩ ጥራት ላይ የተመሰረተ ማድረግ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የምርት ዱካቸዉ የማይታወቅ ወይም ኃላፊነት የሚወስድ አካል የሌላቸዉ ጥራትና ደህንነታቸዉን ስለማሟላታቸዉ ማረጋገጫ የማይቀርብባቸዉ ምርትና አገልግሎቶች በስፋት እንዲሰራጩ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህም የተነሳ የግሉ ዘርፍ ወደ ማምረት ክፍለ ኢኮኖሚ በስፋት እንዳይገባና የደንበኞች ፍላጎትን የሚያረካ ቀጣይነት ያለዉ ኢንቨስትመንት ላይ እንዳያተኩር ከፍተኛ ጫና አሳድሯል፡፡

ይህንን ተግዳሮት ወደ መልካም አጋጣሚ ቀይሮ ፈጣን ዕድገት ለማስመዝገብና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ አገራዊ ምርታማነትን በማሳደግ ለዉጪ ገበያም ሆነ ለአገር ዉስጥ ፍጆታ የሚቀርቡት ምርትና አገልግሎቶች ጥራትና ደህንነታቸዉ የተጠበቀ መሆን ይገባቸዋል፡፡ መንግስት ይህንን እዉን ለማድረግ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማትን በማጠናከር፣ ተቆጣጣሪ አካላትን እንደገና በአዲስ መልክ በማዋቀር፣የትምህርት ተደራሽነትን በማሳደግ ፣የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት እና የዘርፍ

ድጋፍ ሰጪ የምርምር ኢንስቲትዩቶች በተለይም ለጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራዞች በደረጃዎች የተገለፁ የቴክኒክ መስፈርቶችንና መልካም አሰራሮችን እንዲተገብሩ ተግባራዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ ተልዕኮ በመስጠት ጥረት እያደረገ ቢሆንም አገራዊ ተወዳዳሪነትን ለመገንባት ተቀናጅቶ ከመስራት አኳያ ብዙ ይቀራል፡፡

ከዚህ አንፃር የጥራት ፖሊሲው መኖር የልማት እንቅስቃሴዎች በሚከናወኑበት አዉድ ዉስጥ የሚሳተፉ አካላትን እንዲተሳሰሩና እንዲቀናጁ ምቹ መደላድልን ይፈጥራል፡፡

ፖሊሲዉ በጥራት መሰረተ ልማት ስርዓት ዉስጥ የሚኖር ተግባርና ኃላፊነት የማስተሳሰሪያ ሁነኛ መሳሪያ ነዉ፡፡ በስርዓቱ ዉስጥ በቴክኒክ ደንብ ማዕቀፍ የሚካተቱ ህጋዊና አስተዳደራዊ የአፈፃፀም አሰራሮችን ከጥቅም ግጭት የነፃ እንዲሆን፣ የጥራት አገልግሎት አሰጣጥ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኘ፣ደንበኛ ተኮርና ተደራሽ በመሆን የተግባር ድግግሞሽን በማስቀረት ዉስን ሃብትን በቁጠባ ለመጠቀም የማይተካ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጥራት ፖሊሲዉ የቴክኒክ ደንብ ዝግጅትና ትግበራዉ ብሎም የማረጋገጫ ሂደቱ ለንግድ ዕንቅፋት እንዳይሆኑ አሰራር እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡ የጥራት ፖሊሲ ተጠያቂነትንና ተገማች የሆነ መንግስታዊ አሰራርን በማስፈን እና በቀጣይነት የሚሻሻል መልካም አሰራርን እዉን በማድረግ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ወሳኝ ስልት ነዉ፡፡ በዚህም የተነሳ የጥራት መሰረተ ልማት አገልግሎት ፍላጎት ስለሚጨምር የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ይጋብዛል፡፡

በመሆኑም የጥራት ፖሊሲዉ ትግበራ የጥራት ባህልን በመገንባት በተግባር እንዲገለፅና ልማድ እንዲሆን ስለሚያደርግ ተደራጅቶ ግዴታዉን የሚወጣና ጥቅሙን የሚያስጠብቅ ሞጋች ዜጋ ወይም ሸማች ማህበረሰብን በመፍጠር ፍትሃዊ የንግድ ዉድድር ያሰፍናል፣ አገራዊ ምርታማነት ያሳድጋል፣ ኢኖቬሽንን ያበረታታል፡፡ በዚህም የተነሳ የምርትና አገልግሎቶች የገበያ መዳረሻዎች ይበራከታሉ፣ኢኮኖሚያዊ አቅምን በውጤታማነት በመምራት ቀጣይነቱ የተረጋገጠ የስራ እድል በመፍጠር ድህነትን ይቀነሳል፡፡ ስለሆነም የጥራት ፖሊሲ ትግበራ የስኬቱ መገለጫ የምዕተ አመቱን ግቦች ከማሳካት ባሻገር ሀገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ ሃገራት ተርታ እንድትሰለፍ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ፍቱን መሳሪያ ይሆናል፡፡

## 3. የፖሊሲው ተልዕኮ፣ራዕይ፣ ግብ፣ ዓላማ እና መርሆዎች

### *3.1 ራዕይ*

የኢትዮጲያ የጥራት መሰረተ ልማት ስርዓት የዜጎችን የጥራት ባህል በመገንባት፣በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና በሃገራዊ ኢኮኖሚ ላይ ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ልማት በማረጋገጥ በአፍሪካ ቀዳሚ ከሆኑ ሀገራት አንዱ ሆኖ ማየት::

### *3.2 ተልዕኮ*

ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ያለው የጥራት መሰረተ ልማት አገልግሎት በመስጠት እና የተቀናጀና የተናበበ የቴክኒክ ደንብ ማዕቀፍን በመተግበር፣አገራዊ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ

## 3.3 ግቦች

- የኢትዮጵያ ጥራት መሰረተ ልማት ስርአትን በማጠናከር ምርትና አገልግሎቶች ጥራትና ደህንነታቸው ተጠብቆ ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ ለድህነት ቅነሳና ለዘላቂ ልማት አስተዋጽዖ ማበርከት
- ለመንግስትና ለግል ሴክተሩ ምቹ ከባቢን በመፍጠር ጥራትና ደህንነታቸው የተጠበቀ ምርትና አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዲቀርብ ማድረግ
- የኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎት በዓለማቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ተመራጭ እንዲሆኑ ማስቻል
- የዜጎች የጥራት ባህል እንዲጎለብትና እንዲያድግ ማድረግ

## 3.4 ዓላማዎች

### 3.4.1 አጠቃላይ ዓላማ

ምርትና አገልግሎቶች የተጠቃሚውን ፍላጎትና የተቆጣጣሪ አካላትን የቴክኒክ መስፈርቶች፣በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያ እንዲያሟሉ ማድረግ

### 3.4.2 ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ. በተቋማት መካከል ጠንካራ ትስስር በመገንባት የጥራት መሰረተልማት ስርዓት ውጤታማና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠር

ለ. የጥራት መሰረተልማት ተቋማትን ማለትም የስነልክ፣የደረጃ ዝግጅት፣አክሪዲቴሽን እና ተስማሚነት ምዘና የሚሰጡትን አገልግሎት በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅና እንዲኖራቸው አቅማቸውን መገንባት

ሐ. የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ያላቸውን ተግባርና ሃላፊነት በመከለስ ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ማድረግ

መ. ከቀረጥ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ የቴክኒክ ደንብ ቁጥጥር ገደቦች የግብይት ስርዓቱን እንዳያደናቅፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር

ሠ. የዕሴት ሰንሰለትን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ተግባራትን በማከናወን እና የመረጃ ማዕከላትን በመገንባት የቴክኒክ መስፈርቶችንና ብሄራዊ ደረጃዎችን በማሳወቅና በማሰራጨት የሀገር ውስጥ አምራችና አገልግሎት ሰጭዎችን ምርታማነት በማሳደግ በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል

ረ. አዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎችን መቅዳት፣ማላመድና ማመንጨት የሚችሉ የጥናትና ምርምር ተቋማትን መደገፍና ማበረታታት

ሰ. በጥራት ዙሪያ ሰፊ የግንዛቤ ስራ በመስራት ማህበረሰቡና ባለድርሻ አካላት ከጥራት ተቋማት ጋር በጋራ፣በትብብርና በትስስር እንዲሰሩ ማድረግ

ሸ. ብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማቱን የሚያግዝና የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪው በአለም አቀፍ መድረክ ተወዳዳሪ እንዲሆን ብሔራዊ የጥራት ማስፋፊያ ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ

ቀ. የምርቶችን ጥራት የማረጋገጥና የሰርተፊኬሽን ስርአት በመተግበር እና ውጤታማ የቁጥጥር ስርአት በመዘርጋት የሸማቾችን መብት ማስጠበቅ

በ. በቀጣናው፣በአህጉሩና በዓለማቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ መድረኮችና ጉባዔዎች ላይ በመሳተፍ የኢትዮጵያን ጥቅም ማስጠበቅ

## *3.5 እሴቶች እና መርሆዎች*

ለብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ራዕይና ተልዕኮ መሣካት የሚያገለግሉ ህጎች፣ መመሪያዎች እና አሰራሮች አወጣጥና አተገባበር በሚከተሉት መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ መተግበር አለበት።

### የአለም አቀፍ መስፈርቶችን ማሟላት

ፖሊሲው በአጠቃላይ ሁሉም ሃገራዊ የህግ ማእቀፎችና አሰራሮች በተለይም የቴክኒክ ደንብ አፈፃፀም የአሰራር ስርዓቶች በዓለማቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረገባቸን የንግድ ድርድሮች እና ከዓለማቀፍ ንግድ ድርጅት ድንጋጌዎችና ግዴታዎች ጋር የተጣጣሙ እና መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት። ምርትና አገልግሎቶች የዓለም አቀፍ መስፈርትን እና የተቆጣጣሪ አካላት ያስቀመጡትን ግዴታ ስለማሟላታቸዉ በማስረጃ ላይ የተመሰረተና ተቀባይት ያለዉ ማረጋገጫ ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡

### ደንበኛ ተኮር

የጥራት ፖሊሲ ዋነኛ ትኩረቱ ደንበኛዉ በቀጥታ ያስቀመጣቸዉን መስፈርትም ሆነ ያልተገለፁ ነገር ግን በተዘዋዋሪ የሚጠብቃቸዉ ፍላጎቶች ለማርካትና የላቀ ደረጃ ለማድረስ መትጋት እንደሚገባ ያመላክታል፡፡ የሸማቹ ህብረተሰብ ጤንነትና ደህንነትን ለማስጠበቅ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማትና አገልግሎት ጋር የሚመጋገብና የተቀናጀ ቴክኒክ ደንብ አፈፃፀም መኖርን የግድ ይላል፡፡ ለአምራቹና አገልግሎት ሰጪዉም ፍትሃዊ የዉድድር መድረክ እንዲኖር ማስቻልን ያካትታል፡፡ይህ መርህ ለሸማቾች ዕሴት የሚጨምር ድጋፍና አገልግሎት በመስጠት ደህንነታቸዉ የተረጋገጠና ጥራታቸዉን ያሚሉ ምርትና አገልግሎቶች ሳይቆራረጡ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ በማድረግ እርካታቸዉን ማሳደግ ብሎም በተደራጀ ሁኔታ ተሳትፎአቸዉን ማጠናከር ላይ ያተኩራል።

**ቅልጥፍና እና ውጤታማነት**

የምርቶች እና አገልግሎቶች ቅልጥፍና ውጤታማነት የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ እድገት ከሚያመላክቱ መስፈርቶች ዉስጥ ዋነኛዉ ነዉ፡፡ ይህም ምርቶች በብዛት፣ጥራት፣ በአነስተኛ ወጪና ከብክነትና ብክለት ፀድተዉ መመረታቸዉን ያመላክታል፡፡ስለሆነም በግብዓት አጠቃቀም፣ በምርታማነት፣ በጥራት እና በአካባቢ ላይ የሚኖር አሉታዊ ተፅዕኖ መካከል ሚዛናዊነትን መጠበቅ ዋነኛ አላማዉ ነዉ፡፡ለዚህም ስኬት የጥራት ባሕል ግንባታን ከአመለካከት ጀምሮ በተግባር እንዲገለጥ መስራት ምትክ የማይገኝለት ተግባር ነዉ፡፡ ከዚህ አኳያ የህብረተሰቡን፣ የአምራቹንና የአገልግሎት ሰጪዉ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የጥራት መሰረተ ልማት አገልግሎትና ቁጥጥር ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡

**አለማዳላት**

በመደበኛው የንግድ ስርዓት መንግስት ተመሳሳይ ለሆኑ በአገር ዉስጥ ለሚመረቱትም ሆነ ከዉጪ አገር ለሚገቡ ምርትና አገልግሎቶች ያለ ልዩነትና አድልዎ ተመሳሳይ መስፈርትና ቁጥጥር ማድረግ ይገባዋል፡፡

**የተናበበ መስፈርት፣ ቁጥጥርና አሰራር**

መንግሥት በቀጣናዎችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝግጅት፣በመልካም የቁጥጥር ስርዓት ትግበራ፣በሥነ ልክ፣በአክሪዲቴሽን እና በተስማሚነት ምዘና አሰራር ስርአቶች መድረክ ላይ በንቃት በመሳተፍ እና ከነባራዊ ሁኔታዎች በመነሳት የተለየ መስፈርት ማዘጋጀት ካላስፈለገ በስተቀር በዓለም አቀፍ ወይም ቀጠናዊ የወጡትን በመዉሰድ ወይም ፍላጎቱን በመድረኮቹ በማንፀባረቅ ስምምነት ሲደረስበት ወይም አጣጥሞ በመዉሰድ ተግባራዊ በማድረግ ለንግድ ተግባራት እንቅፋት እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

**የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ጥምረት እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ**

መንግስት በጥራት መሰረተ ልማት ስርዓት ህጋዊ ማዕቀፍ፣ አሰራሮች እና ስትራቴጂክ ክፍተት ባለበት የመሪነት ሚና በመጫወት፣ መራሽና ተደራሽ መሆን፣ አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ የግሉ ሴክተር ተዋናዮች ድጋፍና ማበረታቻ ማድረግ፣ ለኢንተርፕራይዞች በእሴት ሰንሰለቱ ላይ በመንተራስ እሴት የሚጨምር ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግን ያካትታል፡፡ የብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ስኬታማ አፈፃፀም ምንም እንኳን የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት ብሎም በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ መጠበቅ ቢሆንም ፍትኃዊ የንግድ ዉድድር እንዲሰፍን በማድረግ አገራዊ ተወዳዳሪነትን ይገነባል፤ ቀጣይነት ያለዉ ልማትን ያረጋግጣል፡፡ ይህ እንዲሳካ የግሉ ሴክተር ምትክ አልባ ሚና ስላለዉ በንቃት እንዲሳተፉ፣ ጥምረት እንዲፈጥሩ፣ ከመንግስት ጋር የመወያያና የመደራደሪያ ቋሚ መድረክ እንዲኖር በማድረግ የባለቤትነት መንፈስ እንዲጠናከርና መሪነቱን እንዲረከቡ የተቀናጀ ጥረት ይደረጋል፡፡

**ጥራትን በዘላቂነት ማረጋገጥ**

ጥራትን በዘላቂነት ማረጋገጥ በፖሊሲ የተቀመሩ አስተዳደራዊ ማዕቀፎችም ሆኑ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች ተለዋዋጭ የሆነ ሶሺዮ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ሁኔታን በመቋቋም ቀጣይነቱን ያረጋገጠ የጥራት መሰረተ ልማት ስርዓት እንዲኖር ማድረግንና ተገቢ የሆነ ሃብት መመደብን ያካትታል፡፡ ይህም መንግስት ህጋዊና ተፈጥሮአዊ ግዴታዉ የሆነዉን የዜጎች ጤንነትና ደህንነት መጠበቅ፣ በንፁህ ቦታና አካባቢ እንዲኖሩ ማስቻልን ያጠቃልላል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የጥራት ፖሊሲ ንግድን ለማቀላጠፍ፣ ዘላቂ ኢኮኖሚ ዕድገትን በማስመዝገብ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለማሳካት ሁነኛ መሳሪያ መሆኑን በመረዳት በተግባር ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ጥራትን በቀጣይነት የማረጋገጥ መርህ መሰረት የጥራት ፖሊሲዉ የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ መነሻ ያደረገና የወደፊት ራዕይ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ሃብት የሚመደብ መሆን አለበት፡፡ ይህንንም ለማሳካት የፖሊሲ ተግባራዊ ማዕቀፎች ፍላጎት መራሽና፣ የምርት ወይም አገልግሎት ዕሴት ሰንሰለትን መሰረት ያደረጉ የጥራት መሰረተ ልማት አገልግሎት መስጠትን፣ ኢንተርፕራይዞችን በመደገፍ አቅም መገንባትን እና መረጃ ማሰራጨትን የሚያካትት ሲሆን መገለጫዎቹም የምርትና አገልግሎት መዳረሻ ገበያዎች መበራከትና በቀጣይነት መሻሻል ዋነኞቹ ናቸው፡፡

## 4. የፖሊሲ መግለጫ

መንግሥት ጥራት ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ መሻሻል፣ለንግድ ሥራ መሳለጥ ፣ ለአካባቢ ደህንነት እንዲሁም ለምርምርና ለፈጠራ ሥራዎች መጠናከር ብሎም ለዘላቂ ልማት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ይገነዘባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥራት በሐገር ዉስጥና በዓለም አቀፍ ገበያዎች የምርትና የአገልግሎቶችን ተቀባይነት የሚያረጋግጥ፣የገበያ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ፣ የዉጪ ንግድ መጠንን የሚጨምር እና የገበያ ድርሻን የሚያሰፋ መሆኑን ያምናል፡፡ የደረጃዎች አተገባበር፣ የተስማሚነት ምዘና ስርዓት፣የቁጥጥር ሥርዓት እና በጥራት ባሕል በበቂ ሁኔታ ባለመዳበራቸው የሀገራችን ምርትና አገልግሎቶች ጥራት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ሁኔታ አዲስ የጥራት ግንዛቤ በመፍጠር፣ጠንካራ የጥራት ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋትና ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር መቀየር አለበት፡፡

በዚህም የተነሳ መንግሥት ፡-

- የምርትና የአገልግሎት አሠጣጥ ጥራትን በማሳደግ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ፣
- ከቀረጥ ውጭ በሚኖሩ ዕገዳዎች የተነሳ ሊደረሱ ያልቻሉትን የገበያ መዳረሻዎች ለመድረስ፣
- የሃገሪቱን ጥራት መሠረተ ልማት ለማጠናከር፣
- የህብረተሰቡን የጥራት ባህል ለማሳደግ፣
- ሁሉንም ሴክተሮች በአገልግሎት አሠጣጥ ጥራት ማንቃት እንዲሁም የሃገር ዉስጥ የግብይት ባህል ደንበኛ ተኮር እንዲሆን ሰፊ የተግባቦት ስራ ለመስራት
- የተቀናጀና የተናበበ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ለመዘርጋትና ለማጠናከር፣
- የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የህብረተሰቡ ጤናና ደህንነት እንዲሁም የአካባቢ ደህንነት ለማረጋገጥ
- ከዓለም አቀፍና ከአህጉራዊ ተሳትፎዎች፣ትብብሮችና ልምዶች ሃገራችን ከፍተኛ ጥቅሞች እንድታገኝ ለማስቻል
- የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች በአጠቃላይ አምራቹ ዘርፍ ደረጃቸዉን የጠበቁ ምርቶች እንዲያመርቱና አገልግሎቶች እንዲሰጡ በመደገፍ በዘርፉ ሃገራዊ ውጤትን ለማስመዝገብ የተለየ ትኩረት ሰጥቷል፡፡

## 5. የፖሊሲው ወሰን

የኢትዮጵያ የጥራት ፖሊሲ የተፈፃሚነት ወሰን የምርትና አገልግሎቶች ጥራት እና የጥራት መሰረተ ልማት ስርዓት ማጠናከር ላይ ያተኩራል፡፡ ፖሊሲዉ የጠራ፣ ዕሴት የሚጨምር አሰራር፣ ዘዴንና ስልትን በመጠቀም በኢኮኖሚዉ ዉስጥ የሚገኙ ተዋናዮች ተቀናጅተዉና ተሳስረዉ በገበያ ዉስጥ የሚገኙ ምርቶችና አገልግሎቶች በብቃት የሚወዳደሩበት ፍትሃዊ የንግድ ስርዓት ምህዳር ይፈጥራል፡፡ ፖሊሲዉ አገራዊ ተወዳዳሪነትን መነሻ በማድረግ ለአገልግሎት ሰጪ፣ ለድጋፍ አድራጊ፣ ለአስፈፃሚ እና ለተቆጣጣሪ አካላት የሚሰጡ ስልጣንና ተግባራት ከዓለማቀፍ አሰራር ጋር የተናበቡ ከጥቅም ግጭት ነፃ የሆኑ፣ ድግግሞሽን ያስወገዱ፣ ግልፅ፣ ተጠያቂነት ያለዉ እና ተገማች አሰራር የሚዘረጋበትን መደላድል መፍጠርን ጭምር ይሸፍናል፡፡ በተጨማሪም ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራትና ደህንነታቸዉን አሟልተዉ ወደ ገበያ የሚገቡበትን፣ የፈጠራ ሥራ የሚበረታታበትን እና ቀጣይነቱ ለተረጋገጠ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበትን ማዕቀፍ አካቷል፡፡

የጥራት የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን በስልጠና፣ በስርዓተ ትምህርት በማካተት ፍላጎት መራሽና እሴት የሚጨምር ድጋፍ ለኢንተርፕራይዞች ወይም ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በማድረግ የጥራት ባህል የሚገነባበት አሰራር ፖሊሲዉ ከሚሸፍናቸዉ ጉልህ ተግባራት አንዱ ነዉ፡፡ ፖሊሲው የማህበረሰቡን ጤንነትና ደህንነት፣የአካባቢና ብዝሃ ህይወት ጥበቃ ፣ ፍትሀዊ ግብይትን በማስጠበቅ ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ የሚገነባበት እንዲሁም የቴክኒክ ደንቦች ለንግድ እንቅፋት እንዳይሆኑ አሰራር ስርዓት መዘርጋትን ያካትታል፡፡ በሌላ በኩል የመከላከያ፣ ፀጥታ እና ደህንነት ተቋማት ተግባራትን ፖሊሲዉ የሚሸፍን ቢሆንም የተቋማቱን የዉስጥ አሰራር ሚስጥራዊነትና ብቃት የሚያረጋግጡበትን አሰራር በሚመለከት ተቋማቱ ራሳቸው በሚዘረጉት ስርአት የሚከናወን ይሆናል፡፡

የጥራት ፖሊሲዉ የግሉ ዘርፍ መሸፈን ያልቻላቸዉን የጥራት መሰረተ ልማት ስርዓት ተግባራት ወሳኝ ክፍተቶች ለመሸፈን በመንግስት ሃብት የሚመደብበት ሁኔታን የሚያመላክት ሲሆን የግሉ ሴክተር ተሳትፎን ማበረታቻና ማትጊያ የፖሊሲዉ አካል ናቸዉ፡፡ በመጨረሻም የጥራት ፖሊሲዉ ከፀደቀበት ጊዜ አንስቶ በስራ ላይ ያሉም ሆኑ ወደፊት የሚወጡ ህጎች ግብአት በመዉሰድ ተጣጥመዉ እንዲዘጋጁና እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

## 6. የፖሊሲ ዋና ጉዳዮች

### *6.1 የምርትና አገልግሎት ጥራት ማሳደግ*

ከዚህ ፖሊሲ ዋና ዋና ግቦች አንዱ ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች አገራዊ፣ ቀጣናዊና ዓለምዓቀፋዊ ደረጃዎችን እንዲያሟሉ በማድረግ ጥራታቸውን ማሳደግ ነው፡፡ የመንግስት አካላት የምርትና አገልግሎቶችን የጥራት መስፈርቶችን በማዘጋጀትና እንዲተገበሩ በማድረግ ይህን ፖሊሲ ያስፋፋሉ እንዲሁም አምራቾችና ተጠቃሚዎች ደረጃዎችንና የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶችን ጥቅም ላይ እንዲያዉሉ ይበረታታሉ፡፡ የቴክኒክ ደንቦችን የመፈፀም አስገዳጅ ስርዓት በሀገሪቱ በቴክኒክ ደንቦች፣ህጎችና አዋጆች የሚደነገግ ይሆናል፡፡የወጪ ምርቶች መዳረሻ አገራት ገዥዎች የተቀመጡ መስፈርቶችን መሰረት አድርጎ ማምረትም ያስፈልጋል፡፡

የምርትና የአገልግሎት ጥራት የሚጀምረው ጥቅሙን ከመረዳት ነው፡፡ በሁሉም የኢኮኖሚ ተዋናዮች የሚገኙ አምራቾችና አገልግሎት ሰጭዎች የምርታቸውንና የአገልግሎታቸውን ጥራትን ማረጋገጣቸው የሚያስገኘውን የተወዳዳሪነትና ገበያ ጥቅም መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ በሀገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ ትላልቅ አምራች ድርጅቶች ፣መካከለኛ፣አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሀገሪቱን ደረጃ እንዲተገብሩ ድጋፍ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ አገልግሎት ሰጭ የመንግስት ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ሌሎች ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ አገልግሎት ሰጭዎች እና የግል አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ደረጃዎችን ስለመጠቀም፣ የምርትና አገልግሎት ጥራት እንዲጎለዘቡ ማድረግና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ይህንን በትኩረትና በትጋት በመስራት የአገሪቱን ዘላቂና ፈጣን ዕድገት ዕውን ማድረግ ይቻላል፡፡

## 6.2 *የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማትን ማጎልበት*

የመንግስታዊና የግሉን ዘርፍ ተቋማዊ ማዕቀፍ የሚያካትተው የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ፡- የደረጃ ዝግጅትና ትግበራ፤ የኢንዱስትሪ፣ሳይንሳዊና ሕጋዊ ሥነልክን የሚያካትተውን የሥነልክ አግልግሎት፣ የአክሬዲቴሽን እንዲሁም በተቆጣጣሪ አካላት እና በገበያው የሚጠየቁ የምርትና አገልገሎቶች ተፈላጊ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ተቀባይነት ያለው የምስክርነት ሰርተፊኬት ለመስጠትና አስፈላጊ የሆኑ ማስራጃዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ የኢንስፔክሽን፣ፍተሻ፤ ሰርቲፊኬሽንና ካሊብሬሽን የሚጨምረው የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶችን የሚያካትት ይሆናል፡፡

የጥራት መሰረተ ልማት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለምርትና አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ለተጠቃሚዎችና ለተቆጣጣሪ አካላት ተገቢዉን አገልገሎት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በእነዚህ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች እንደ አሰፈላጊነቱ በግል ዘርፉም የሚከናወኑ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

መንግስት ጠንካራ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳደሪ የሆኑ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማትን መገንባት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም መንግስት ጥራት መሰረተ ልማት መዋቅር ምህዳርን ለማስፋት በቂ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን ፤ለተቋማቱ ባለሙያዎች ስልጠናዎች፣ ዎርክሾች እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች የሚያስፈልጉ የገንዘብ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የጥራት ቁጥጥር እና የተስማሚነት ምዘና ስራ የሚሰሩ ባለሙያዎች ስራዉን ለመስራት የሚያስፈልገውን እውቀት፣ ክህሎትና ስነምግባር እንዲኖራችው የሚያስችል የአሰራር ስርአት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

አገሪቱን ለከፍተኛ ወጭ እየዳረገ የሚገኘውና ለጥራት ችግር አንዱ ምክንያት የሆነው የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና ማዕከልን በተሟላ መልኩ ለማቋቋምና አቅም ለመገንባት መንግስት በትኩረት ይሰራል፡፡

### 6.2.1 *ደረጃዎች*

በኩባንያዎች እና በሌሎች ዘርፎች የሚዘጋጁ የግል ደረጃዎች ዝግጅት በብሔራዊ የደረጃ ተቋም ሊደገፍ ይገባል፡፡ ከብሔራዊ የደረጃ ዝግጅት ሂደት ዉጪ የተዘጋጁ የግል ደረጃዎች በችርቻሮ ንግድ ዘርፍ ያሉ ድርጅቶች በስፋት ጥቅም ላይ እያዋሉት ስለሆነ በዓለማቀፉ ንግድ ዉስጥ በጣም ተፈላጊ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የደረጃ ተቋም ኢንዱስትሪዎችና አምራቾች አተገባበር ላይ እንዳይቸገሩ እነዚህ የግል ደረጃዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ለማሳካት መንግስት፡-

1) በሁሉም ደረጃ በሚያዘጋጁ አካላት መካከል ለእቅድ፣ ለእርስ በርስ ግንኙነት እና መስተጋብር ግልፅ የሆነ ቅንጅትና ትብብር ይፈጥራል፣

2) ብሔራዊ የደረጃዎች ተቋምን የደረጃዎችን ስራ በማስተባበር እንደ ዋና ተቋም እና እንደ ብቸኛ የብሔራዊ ደረጃዎች መገኛ አካል አድርጎ ይሰይማል ኃላፊነትን ይሰጣል፣

3) ነባሩን የደረጃዎች ህግ ከዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮ ጋር በሚጣጣም መልኩ መከለስ እና በደረጃዎችና ተዛማጅ ተቋማት መካከል ያለዉን ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጠናከር ያደርጋል፣

4) ለደረጃዎች ዝግጅትና ትግበራ ስራዎች ቅድሚያ የሚሰጥባቸዉን አሰራሮች ይቀይሳል

### 6.2.2 ስነ ልክ

**ሳይንሳዊ ስነልክ**

*ሀ. ብሔራዊ የስነ ልክ ተቋም በሳይንሳዊና በኢንዱስትሪያዊ ስነ ልክ መስፈርቶች ላይ ይሰራል። መንግስት ብሔራዊ የልኬት ደረጃዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣናትን ኢንዱስትሪዉ በሚፈለዉ ልክ እዉን እንዲሆኑ ለማስቻል የተቋማቱ አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፡፡*

*ለ. መንግስት በኢትዮጵያ ዉስጥ በሁሉም መስክ ተአማኒና ትክክለኛ የልኬት አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ ብሔራዊ የልኬት ደረጃዎችን ጠቃሚ በሆነ ሳይንሳዊ የስነልክ ስርዓት በተለየ የልኬት መስክ (ለምሳሌ በኬሚስትሪ፣ ጨረራ፣ቫይሮሎጂ እና በመሳሰሉት) በቴክኒክ ብቁ ሆነዉ ወደ ተሰየሙ ሌሎች ብሔራዊ ተቋማት ሊያስፋፉ ይችላል::*

*ሐ. የተሰየሙ ተቋማትን የመገንባት ሂደት ኃላፊነት በተሰጠዉ ሚኒስቴር መ/ቤት እና በተሰየመዉ ተቋም እንዲሁም ተቋማቱ ተጠሪ በሆኑባቸው ሚኒስቴር መ/ቤት መካከል የሚደረግ ስምምነት ይሆናል፡፡ በስነልክ ተቋማት መካከል ተገቢ የሆነ ትብብርን ለማረጋገጥ ይህ ስምምነት የሌለዉ የተሰየመ ተቋም ሊኖር አይገባም፡፡ በBIPM መልካም የአሰራር ልምድ መሰረት ብሄራዊ የስነ ልክ ተቋሙ የራሱንና ሌሎች የተሰየሙ የስነልክ ተቋማት ከCIPM ጋር ባለው የጋራ እውቅና ስምምነት መስፈርት መሰረት የስራ አመራር ስርአት መዘርጋታቸውን ያረጋግጣል። ከአለም አቀፉ ተቋም (BIPM)፣ ቀጠናዊ ተቋማት (RMOs) እና ሌሎች በሚኖር ትብብር ብሄራዊ የስነልክ ተቋሙ የሀገሪቱን የልኬት ደረጃ ተዋረዳዊ ትስስር ያረጋግጣል፡፡*

*መ. የብሔራዊ የስነ ልክ ተቋም እና ሁሉም ለጉዳዩ የተሰየሙ ተቋማት የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፎች እና ተቆጣጣሪ አካላት ያሏዋቸውን ፍላጎቶች በጥንቃቄ መያዝና ከኋላፊነት ድርሻቸው አኳያ ከዓለም አቀፍ ስነ ልክ ሥርዐት ጋር መናበብና መተሳሰር*

ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ትስስር በልኬት ንጽጽር እና የልኬታ አካላት ችሎታቸው አማካይነት በዓለም አቀፍ እውቅና ሥርዐት ውስጥ (ማለትም ቁልፍ የማነፃፀሪያ መረጃ ቋት) በዋናነት በBIPM የሚታይ ይሆናል፡፡

**የኢንዱስትሪ ሜትሮሎጂ**

ሀ) በአገራዊ የሜትሮሎጂ ተቋም ከሚጠበቀው አገራዊ የልኬት ደረጃዎች ጋር የሚኖርን የእርከን ተዋረዳዊ ትስስርን (Traceability) ጠብቀው ካሊበሬት እስከተደረጉ ድረስ የካሊብሬሽን አገልግሎቶች በአገራዊ የሜትሮሎጂ አካላት እንዲሁም የመንግስት ወይም የግል በሆኑ የካሊብሬሽን ቤተሙከራዎች፣ ብቃታቸው ዕውቅና ኖሮት በተሰይሙ የአገር ዉስጥ ወይም በውጭ ሀጋራት በሚገኙ ተቋማ ሊሰጡ የሚችሉ ሲሆን

ለ) አገራዊ ልኬቶች በንግድና ህግ ማስፈጸም ተቀባይነት እንዲኖራቸው በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የካሊብሬሽን አገልግሎቶች ለኢንዱትሪዎች፣ ለተቆጣጣሪዎች፣ ለህብረተሰብ  ከተቀመጡ አገራዊ የልኬት ደረጃዎች ጋር በማስተሳሰር ተዋረዳዊ ትስስሩን እንዲጠብቁ አገራዊ የስነ ልክ አካሉ በትጋት ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**የሣይሳዊ መሳሪያዎች ጥገና**

አገራዊ የስነ ልክ ተቋሙ በሣይሳዊ መሳሪያዎች  በግዢ፣  በጥገና፣  በማስወገድ እና  በመሳሰሉት የስልጠናና የማማከር አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ ለሌሎች የሣይንሳዊ መሳሪያዎች ጥገና ተቋማት ድጋፍ ይሰጣል፡፡

### 6.2.3 አክሪዲቴሽን

መንግስት የተስማሚነት ምዘና አካላት ብቃታቸው በአክሪዲቴሽን ተቋም እንዲረጋገጥ ያበረታታል ይደግፋል፡፡ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት ለማሟላት የፍተሻና የኢንስፔክሽን ስራዎች የአክሪዲቴሽን ዕውቅና ባለው ወይም ውክልና በተሰጣችው የተስማሚነት ምዘና አካላት ይሰጣል፤ ብሄራዊ የአክሪዲቴሺን ተቋም የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት የአክሪዲቴሽን ዕውቅና ይሰጣል። የመንግስታዊ ተቋማትን አቅም ከመገንባት ጎን ለጎን መንግስት የግል የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት የሚሰጡ አካላት እንዲበረታቱና እንዲጎለበቱ የሚያስችል አሰራር ያወጣል፤ተቆጣጣሪ አካላትም  የግል የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ሰጪ አካላት የአገልግሎት ብቃታቸው በአክሪዲቴሽን ተቋም እስከተረጋገጠ ድረስ ለመንግስታዊ ግዢ፤ ቴክኒክ ደንብ ለማስከበር ሊጠቀሙበት ይችላሉ።  መንግስት የፍተሻ ላቦራቶሪዎች የሚያወጧቸዉ የምርት ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች በዓለማቀፍ ደረጃ ተአማኒነት እንዲኖራቸዉ እና ለላኪዎች፣ለአስመጪዎች እንዲሁም ለምርቶቹ ተጠቃሚዎች ማስተማመኛ ለመስጠት የፍተሻ ላቦራቶሪዎችን የአክሪዲቴሺን ዕውቅና ማግኘትን ያበረታታል፡፡ ብሔራዊ የአክሪዲቴሽን ተቋም በሀገሪቱ ዉስጥ ያሉ የተስማሚነት ምዘና የሚሰጡ አካላትን በመመዝገብ መረጃ ያደራጃል፡፡

### 6.2.4 ተስማሚነት ምዘና

እንደ ኢንስፔክሽን፣ፍተሻ፤ሰርቲፊኬሽንና ካሊብሬሽን የመሳሰሉት የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶች  ተገቢውን አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ደረጃዎች በሚያሟሉ በመንግስታዊም ሆነ በግሉ ዘርፍ በሚገኙ ቤተሙከራዎች፤የኢንስፔክሽን አካላት፤ የሰርተፊኬሽን አካላት፤ በካሊብሬሽንና ሌሎች ቤተሙከራዎች ወይም የአክሬዲቴሽን ዕውቅና ባላቸው በመንግስት በተሰየሙ ወይም ዓለምአቀፍ ተቋማት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ሰጭዎች የሬጉላቶሪ ቁጥጥርን ህግ በማስፈፀም ስራ ወሳኝ ሚና ያላቸው ሲሆኑ የግድ አስፈላጊ የሆኑ ከፍተኛ ቴክኒክ ደጋፊ አካል ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ቀልጣፋና ውጤታማ

የተስማሚነት ምዘና አገልግሎትን ለማረጋገጥ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ሰጭዎች አቅም ማሳደግ የግድ ይሆናል፡፡ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ሰጭዎች ፋሲሊቲዎችና ግብአቶች እንደገበያው ፍላጎትና መስፈርት ማደግና መዘመን ይኖርባቸዋል፡፡ በአለምአቀፍ ደረጃዎች የአክሬዲቴሽን ዕውቅና እንዲያገኙና በተመጣጣኝ ክፍያ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ሰጭዎች በኢንዱስትሪ ክላስተሮች አካባቢ መደራጀታቸው የተለያዩ አምራች ክፍሎችን ለማጠናከርና ምርታማነትን ለማሳደግ ያስችላል፡፡ በመንግስት አካላትና የተደራጁ ላቦራቶሪዎችና በሌሎች ዘርፍ የሚገኙ ላቦራቶሪዎችን ወደ አገራዊ የንጽጽር ቤተሙከራነት እንዲያድጉ እና እንደ አስፈላጊነቱ የማነጻጸሪያ ስታንዳርዶችንና ቁሶችን እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡ እነዚህ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶች ለምርቶችና አገልግሎቶች ቅርብ በመሆን የፍተሻ ውጤቶች በጊዜው እንዲደርሱ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 6.2.5 የቴክኒክ ደንብ

የቴክኒክ ደንቦች ጤናን፣ ደህንነትን፣ የአካባቢ ጥበቃንና ጤናማ የንግድ ስርዓትን ለማረጋጋጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በአዋጆችና በቴክኒክ ደንቦች ህግን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ግልፅ ትርጓሜዎችና የህግ የሥነስርዓት ድንጋጌዎች ሊካተቱ ይገባል፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቶች እና በሌሎች አግባብ ያላቸው የመንግስት አካላት በስራ ላይ ያሉ የቴክኒክ ደንቦች ከአለም ዓቀፍ የንግድ መስፈርቶችና ስምምነቶች አንጻር መገምገም፣ መከለስና መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡

የመንግስት አካላት በቴክኒክ ደንቦች አማካኝነት ጤናን፣ ደህንነትን፣ የአካባቢ ጥበቃንና እና የሸማቹን ሙብት መጠበቅን ዓላማ ያደረጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን ያወጣሉ፡፡ እነዚህ ደንቦች ህብረተሰቡን ወይም አለም ዓቀፍ መስፈርቶችን ማዕከል ባደረገ በተወሰነ መደበኛ የጊዜ ገደብ ይከለሳሉ፡፡

በቴክኒክ ደንቦች አወጣጥና አተገባበር ላይ ወጥና ግልጽ የሆነ አሰራር ለማስፈን መንግስት የማስተባባርና የማቀናጀት መንገዶችን ይቀይሳል፡፡

የቴክኒክ ደንቦች አገራዊ ቀጣናዊና አለም አቀፍ ደረጃዎችን መሰረት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ደንቦች ልዩ አገራዊ ሁኔታዎችን እሳቤ ውስጥ የሚያስገቡ ቢሆንም ቀጣናዊ የትስስር መስፈርቶችን፣ የሳኒተሪና ፋይቶ ሳኒተሪ እንዲሁም የንግድ የቴክኒክ ገደቦችን የሚመለከቱ የአለም የንግድ ድርጅትን ስምምነቶች መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡

ሁሉም የቴክኒክ ደንቦች ተመዝግበው በተደራጀ ሁኔታ መያዝ ያለባቸው ሲሆን የአስተዳደር ስርዓት ሊታቀድላቸው ይገባል፡ ፡ በመሆኑም የሚከተሉት ለገበያ ላይ ክትትል፣ ለኢንስፔክሽንና የህግ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ሀ) ምርቶች የተቆጣጣሪ አካላትን ወደ ገበያ የመግባት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው እንደ የምርቶቹ ዓይነትና ሊያስከትሉት የሚችሉት አደጋ ከፍ ያለ ሲሆን ብቻ ነው፡፡በሁሉም ሁኔታዎች በገበያ ላይ ክትትል እና የህግ እርምጃ መውሰድ የተቆጣጣሪ አካላት ኃላፊነት ይሆናል፡፡

ለ)የቴክኒክ ደንቦች የወጣላቸው ምርቶች የገበያ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ወደ ገበያ በሚገቡበት ወቅት የማምረቻ፣ ንግድና የመጋዘን ቦታዎችን መመልከትን ይጨምራል፤እንዲሁም ምርቶች ለግልጋሎት የሚዉሉባቸውንና ሌሎች መገበያያዎችን ይጨምራል፡፡ የገበያ ክትትልና የቁጥጥር እርምጃዎች የተመጣጣኝነት መርህን፣ ማለትም ሊያስከትል ከሚችለው አደጋና ከመስፈርት የመውረድ አኳያ፣ የተመዘኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ሐ) አቅራቢዎች በስራ ላይ ያሉ የቴክኒክ ደንብ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በቀጣይነት ለማረጋገጥ ህጋዊ እርምጃዎች አስፈላጊ ይሆናሉ፡፡ አቅራቢዎች የቅጣት እርምጃ ሳይወሰድባቸው በራሳቸው የደረጃ መስፈርትን የማያሟሉ ወይም የጥራት ጉድለት ያለባቸውን ምርቶችንና አገልግሎቶች መለየትና ከገበያ ማስወገድ እንዲችሉ የሚያደርግ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ስራ ላይ የማዋል ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡ አቅራቢዎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ስራ ላይ ሳያዉሉ የቀሩ እንደሆነ የህግ እርምጃ ኢንዲወሰድባቸው የሚያስችሉ ድንጋጌዎች እንዲኖሯቸው ይደረጋል፡፡ ተቆጣጣሪ አካላት በራሳቸው በአቅራቢዎች ላይ ገንዘብ ቅጣት መጣል አይችሉም፡፡

መንግስት የህጋዊ ስነልክን ጨምሮ የቴክኒክ ደንቦችን የሚያስፈጽሙ ተቆጣጣሪ አካላት እና በብሄራዊ የቴክኒክ ደንብ ተቆጣጣሪ አካላት የሚተገበሩ የቴክኒክ ደንቦችን አፈጻጸም የሚያስተባበርና የሚመራ ተቆጣጣሪ ተቋም ያቋቁማል፡፡ ብሄራዊ የቴክኒክ ደንብ ተቆጣጣሪ አካላት ነጻና ሙሉ ስልጣን የሚኖራቸው ሲሆን ጤናን፣ ደህንነትን፣ አካባቢን ከደረጃ በታች ከሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች ለመጠበቅ የኢንስፔክሽን ስራዎችን የማከናወን ስልጣንና ሃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡ ኢንስፔክተሮች ደንቦችን ለማስከበር የቴክኒክ ደንብ መስፈርቶችን/አስገዳጅ ደረጃዎችን መሰረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በኢንስፔክተሮች የተለዩ የቴክኒክ ደንብ መስፈርቶችን ወይም አስገዳጅ ደረጃን ካለማሟላት ጋር የተያያዙ ህግ የማስከበር ስራዎች በተቆጣጣሪ አካላቱ የሚወሰድ እርምጃ ይሆናል፡፡

### 6.2.6 ህጋዊ ሥነ ልክ

ሀ) መንግስት በንግዱ እንቅስቃሴ፣ በህግ ማስከበር፣ በጤና አገልግሎቶች እንዲሁም በአካባቢ ጥበቃ የሚሰራባቸው ልኬቶች የህጋዊ ሥነልክ ስርዓት ሆነው እንዲወጡ ያደርጋል፡፡

ለ) በመለኪያ መሳሪያዎችና ቅድመ እሽግ ምርቶች ላይ የሚወጡ የቁጥጥር ድንጋጌዎች በተቻለ መጠን የህጋዊ ሥነልክ ዓለምአቀፍ ድርጅትን(OIML)፣ ዓለምአቀፍ የደረጃዎች ድርጅት(ISO)፣ ወይም ዓለምአቀፍ የኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን (IEC) የሚቀርቡ ምክረ ሃሳቦችን መሰረት ያደርጋሉ፡፡

ሐ) ውጤታማ የህጋዊ ሥነልክ ህግ የማስከበር እውን እንዲሆን መንግስት ህጋዊ ሥነልክን የማቋቋምና ብቁ ሆነው ዕውቅና ያለው የቁጥጥር ስራ እንዲሰሩ ተገቢዉን ሀብትና የሰለጠነ የሰው ሃይል ይመድባል፡፡

### *6.3 ሀገራዊ የጥራት ባህል ግንባታ*

የብሄራዊ ጥራት ፖሊሲ የጥራት ባህል በማስተዋወቅ የሸማቹን መብት ጥበቃ ያረጋግጣል፡፡መንግስት ባለድርሻ አካላት ትምህርትና ስልጠና የሚያገኙበትን አጋጣሚ በመፍጠር ካለውና ከመጭው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር አብረው መራመድ እንዲችሉ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

መንግስት ሸማቾች ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት የመጠየቅ ልምድ እንዲያዳብሩ የሚያስችል ባህል ለመፍጠር በሃላፊነት ይሰራል፡፡

መንግስት የጥራት ፖሊሲውን በመምራትና ትግበራውን በማረጋገጥ በአምራቹ፣ በአገልግሎት ሰጪው፣ በተጠቃሚው፣ በአስመጪና ላኪው በተቆጣጣሪው አካላትና በማህበረሰቡ ለጥራት ያለው ግንዛቤ እንዲጨምር በማድረግ የጥራት ባህል እንዲሰርጽ ይሰራል፡፡

የጥራት ባህልን ለመገንባት መንግስት ጥራትን የማስተዋወቅ ስራ ይደግፋል፣ የጥራት ስራ አመራር በመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲተገበር ያቀናጃል፣ በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጥራትን በተመለከት ግንዛቤ ማስጨበጥና የእውቀት ሽግግር ላይ እንዲሰራ የአሰራር ዘዴ ይቀይሳል ይደግፋል፤

መንግስት የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት በማህበረሰቡ የጥራት ጽንሰ ሀሳብ ለማስረጽ የሚያደርጉትን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በደረጃና በጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት የሚሰጡ ትምህርቶችን ያበረታታል፡፡ መንግስት የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት በደረጃ፣ በስነልክ፣ በአክሪዲቴሽንና በተስማሚነት ምዘና ላይ ለተለያዩ አካላት የሚያደርጉትን የመረጃ ልውውጥና ግንዛቤ ማስጨበጫ ይደግፋል፡፡

ተቆጣጣሪ አካላት መልካም የቁጥጥር ስርአትን ፣ የቁጥጥር ተፅዕኖ ግምግማንና ሌሎች መርሆዎችን እንዲገነዘቡና እንዲተገብሩ መንግስት በቴክኒክ ደንብ ማዕቀፍ መመሪያ ሰነድ ላይ ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫና ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፡፡ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ መልካም ተሞክሮዎችን ለሀገር ኢኮኖሚ፣ ባህል፣ ደህንነትና ሌሎችም ጉዳዮች በሚጠቅሙ መልኩ በአገር አቀፍና በአለም አቀፍ ደረጃ መሰረት እንዲቀመሩ፤ እንዲተገብሩና እንዲያሳድጉ ይበረታታሉ፡፡

የመንግስትና የግል የትምህርት ተቋማት የጥራት ባህልን ለማሻሻልና የጥራት ፖሊሲውን ለመተግበር የሚያስፈልግ እውቀትና ክህሎት የሚያስጨብጡ የትምህርት ፕሮግራም ይተገብራሉ። ይሄም የኦዲተሮች፣ የጥራት ስራ አመራር ስርአት፣ የአካባቢ ስራ አመራር ስርአት፣ የስራ ቦታ ጤና እና ደህንነት አማካሪዎችንም ይጨምራል፡፡ መንግስት የጥራት መሰረተ ልማት አግልግሎቶች በሁሉም ደረጃዎች በካሪኩለም ተቀርጽው እንዲሰጡ ይደግፋል።

ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲውን መቅረጽ የመንግስት ሃላፊነት ቢሆንም መተግበር ግን የመንግስት ኃላፊነት ብቻ አይደለም። በመሆኑም የግሉ ዘርፍም ሆነ ማህበራት እኩል ኃላፊነት አለባቸው። ይህ የጥራት ፖሊሲ ሁሉም ስራዎች ወደ ልህቀት

እንዲሻገሩ፣ ሀገር በቀል ምርቶችና አገልግሎቶች በአለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነት እንዲያገኙና ዜጎች በሀገር ውስጥ አምራቾችና ምርቶች እምነት እንዲኖራቸው የሚረዱ የማበረታቻ ዘዴዎችን መጠቀምን ያበረታታል። መንግስትና የክልል ተቆጣጣሪ አካላት የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማትን አገልግሎት የመንግስት ግዥ ለመፈፀምና የምርትና አገልግሎቶችን ጥራት ለማስጠበቅ ይጠቀማሉ።

መንግስት የሸማቾች መብት ጥበቃ ማህበራት ሸማቾች ደረጃቸውን ካልጠበቁ እና ጎጂ ምርቶች እንዲሁም ከአሳሳች ማስታወቂያዎች እንዲጠበቁ የሚሰሩትን የሸማቾች መብት ጥበቃ ስራዎችን ይደግፋል፡፡

በአለም አቀፉ ንግድ የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት አስፈላጊነቱ በአለማቀፍ ንግድ እድገት እየተገለጸ መጥቷል። የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት በአለም አቀፍ ግብይት እውቀትና ቴክኖሎጂ በተመረኮዙ ምርቶች ላይ በጉልህ ይታያል። በአለም አቀፉ የንግድ ድርጅት ንግድ ተኮር የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ድርጅቱን ለመቀላቀል የተቀመጠ ዝቅተኛው መስፈርት ነው። ስለዚህ ይህ የጥራት ፖሊሲ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃን በመደገፍ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ በአጋርነት መስራትን ለማሻሻልና ወደ አለም አቀፍ ገበያ ለመግባት ያስችላል።

### *6.4 ጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች (MSME)*

ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በሀገራችን ንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። በመሆኑም መንግስት በጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ የጥራት አስተዳደር ስርዓቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እና የምርታቸውን ጥራት ለማሳደግ እንዲችሉ እንዲሁም በሀገሪቱ የጥራት ባህል እንዲያድግ የበኩላቸውን ሚና እንዲዎጡ ማበረታቻዎችን እና ድጋፎችን ያደርጋል፡፡

በመንግስት የሚሰጠው ድጋፍ የጥራት መስፈርቶችን በሚያሳይ መልኩ ካሟሉ ማበረታቻ እና ሽልማትን ያካትታል። የቴክኒካል ደንቦችን መስፈርት በሚወሰንበት ጊዜ መንግሥት ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ዝቅ ማድረግ ወይም ወደ ሰፊ የማታለል ተግባር እንደማይወስድ ከተረጋገጠ እና የጤና እና የደህንነት ጉዳዮች የማይመለከት ከሆነ ሙሉ ለሙሉ በማንሳት በሂደት እንዲያሟሉ እንዲበረታቱ ይደረጋል።

### *6.5 ቅንጅትና ትብብር*

የብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ብቻውን ምንም ሊፈይድ አይችልም፡፡የቴክኒክ ደንቦችን ማክበርን ጨምሮ ደረጃዎች ፣ ብሔራዊ ስነ-ልክ ፣ የተስማሚነት ምዘና ድርጅቶች እና ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ከተመለከቱ በርካታ ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት ፡፡ በዚህ ረገድ ዋናው ዓላማ በጥራት መሠረተ-ልማት መካከል ሁለንተናዊ ቅንጅት በመፍጠር የተቀላጠፈ እና አርኪ አገልግሎት በጥራት መስጠት ነው፡፡ በተለያዩ ተቆጣጣሪ አካላት የሚኖረው ውጤታማ ቅንጅት በቁጥጥር ስርአት ውስጥ ያሉትን ክፍተቶች በመድፈንና የስራ ድግግሞሽ እንዲቀንስ / እንዲጠፉ በማድረግ የተስናሰለ የቁጥጥር ስርአት ማስፈን ነው።

### 6.5.1 ቅንጅት እና የፖሊሲ ሁኔታ

የመንግስት ተቋማትን እንቅስቃሴ ማስተባበር ማለት በተቋማቱና በፖሊሲዎቻቸው መካከል የተሻለ ግንኙነት (ለምሳሌ የምግብ ደህንነት ፖሊሲ ፣ የጤና ፖሊሲ ፣ የግብርና ፖሊሲ ፣የደንበኞች ፖሊሲ ፣ የንግድ ፖሊሲ ፣ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ፣ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ፣ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ወዘተ) እንዲኖር ማድረግ ማለት ነው ፡፡

ከብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ጋር በተያያዘ መንግስታዊና የግል አካላትን እንቅስቃሴ ማስተባበር በብሔራዊ የጥራት ምክር ቤት ይከናወናል ፣ አቋሙ ፣ እንቅስቃሴው እና አወቃቀሩ በተደነገገው ሕግ ይተዳደራል ፡፡

### 6.5.2 አለም አቀፍና ቀጣናዊ የጥራት መሰረተ ልማት

የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት አደረጃጀት የሀገሪቱን፤የቀጠናውንና የአለም አቀፍ መስፈርቶችን ለማሟላት ሲሆን፣ ይሄም ተቋማቱ ለሚሰጡት አገልግሎት እውቅና እንዲኖረው በማድረግ የሀገሪቱን ንግድ ያሳልጣል። ኢትዮጵያ በርካታ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶችን እና ፕሮቶኮሎችን ማክበር ስላለባት ፖሊሲው ከሀገር ውስጥ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ጋር መቀናጀት ብቻ ሳይሆን ዙሪያ ገባውን የፖሊሲ አከባቢ ከሀገሪቱ የውጭ ግዴታዎች ጋር በውጤታማነት በማስተሳሰር እነዚህን የውጭ አካላት እንድትከተል ማመቻቸት ይኖርበታል ፡፡

መንግስት የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማቱም ሆነ ሌሎችም ተዛማጅ የስራ ዘርፍ ላይ ያሉ ተቋማት ዘርፉን በተመለከተ በሚደረጉ አለም አቀፍም ሆነ ቀጠናዊ ጉባኤዎች ላይ እንዲሳተፉ በቁርጠኝነት ይደግፋል። ሀገሪቱ በአለም አቀፍም ሆነ በቀጠናዊ ጉባኤዎች ላይ የምታደርገው ተሳትፎ በአለም አቀፍ የልማት አጋሮችና በግሉ ሴክተርም እንዲደገፍ ይጠበቃል።

### 6.5.3 በብሔራዊ የጥራት ምክር ቤት

ምክር ቤቱ የብሄራዊ የጥራት ፖሊሲን ለማስፈፀም ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት አጠቃላይ የዘርፉን የጥራት ተነሳሽነትና ስትራቴጂዎች የሚያራምድ ይሆናል፡፡ የብሔራዊ ጥራት ምክር ቤት አወቃቀር ከመንግሥትና ከግል ኢኮኖሚና ከማኅበረተሰብ ዘርፎች የተውጣጡ ቁልፍ ተዋንያን ያካተተና ሁሉን አቀፍ ውክልናን የሚሳይ ይሆናል፡፡ ምክር ቤቱ በጥራት መሰረተ ልማት ስርአት ውስጥ ያለውን ሂደት የማስተባበር፣ የመከታተልና የመደገፍ ሀላፊነት ይኖርበታል።

### 6.5.4 የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ፎረም

መንግስት ባለድርሻ አካላት ተሰባስበው በጥራትና ደረጃ ጉዳይ የሚመክሩበትንና ለመንግስት ዘርፉን ለማሻሻል በሚያስፈልጉ የፖሊሲ ማሻሻያ ጉዳዮች ላይ ምክር የሚሰጡበትን መድረክ/ ፎረም ይደግፋል፤ መንግስት በጥራት ዙሪያ የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ ለማቅረብና የጥራት መሰረተ ልማት ስትራቴጂው ውጤታማ ሆኖ እንዲተገበር የሚያገለግል የጥራት መሰረተ ልማት መድረክ/ፎረምን መመስራትና ዘላቂነቱን በቁርጥኝነት ይደግፋል፡፡

### 6.5.5 የቴክኒክ ደንብ ማስተባበር

ውጤታማ የቴክኒክ ደንብ ትግበራ ስርአት ለማምጣትና ብሎም ተገማች የቴክኒክ ደንብ ስርአት ለማስፈን በቴክኒክ ደንብ አስፈጻሚ አካላት መካከል ውጤታማ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር ያስፈልጋል።

በቴክኒክ ደንብ አፈጻጸም ክፍተት እንዳይኖር፣ ተደራራቢ ቁጥጥር እንዳይኖር፣ የቁጥጥር ድግግሞሽ እንዳይኖር ወይም በተለያዩ ተቆጣጣሪ አካላት የጥቅም ግጭት እንዳይኖር መንግስት በተቆጣጣሪ አካላት መካከል ውጤታማ ቅንጅት እንዲኖር አመራር በመስጠት ቁርጠኝነቱን ያሳያል። በተቆጣጣሪ አካላት መካከል የሚኖር ትብብር የቁጥጥር ክፍተቶችንም ሆነ መደራረቦች ይቀንሳል፤ እንዲህ አይነቱ ትብብር በተቆጣጣሪ አካላት መካከል የሚኖሩ የሃላፊነት ባለቤትነት ግጭቶችን አስወግዶ የጥራት መሰረተ ልማት ትግበራው የተዋሃደና የተበታተነ የቁጥጥር ስራን ያስውግዳል።

## *6.6 ጥራትና ዘላቂ ልማት*

*የምንፈልገው መፃኢ ጊዜ ድህነት እንዲወገድ ፣ የፍጆታ እና ምርት እድገት ቀጣይነት እንድኖረዉ እንዲሁም ለተፈጠሮ ሃብት ጥበቃ እና አመራር ተወራራሽ ዓላማዎች እና ቀጣይነት ላለው አስፈላጊ የልማት መስፈርቶች ትኩረት ሰጥቶ መስራት ለዘላቅ ልማት መረጋገጥና ጥራት ወሳኝ ነዉ:: ልማትን በልማዳዊ መንገድ ማከናወን ከሚያስከትለው አሉታዊ ውጤቶች መካከል አንዱ ዘላቂነት የሌለው የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ነው::ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲዉ ቀጣዩ ትዉልድ ፍላጎቱን ለማሳካት እና ለሕዝብ ጤና መሻሻል እና የኑሮ ደረጃ እድገት አበርክቶ እንዲያደርግ እና ይህንንም ለድርድር አለማቅረብን የተመለከተ ሥነ ምግባር የሚደርስ ቀጣይነት ያለውን የአሠራር ማዕቀፍ ዒላማ ለመጨበጥ እና ማህበራዊ እና ምጣኔ ሃብታዊ ልማትን ለማሳካት ያለመ ነው :: እንዲሁም የጥራት ፖሊሲው ቀጣይ ልማት በጥራት እንድረጋገጥ ፣ ለተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ውጤታማነት እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመዋጋት ከብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት -ጋር የተዛመዱ ተቋማትን ቅንጅት በመርህ ለመምራት ያግዛል::*

*በዚህ ረገድ የዓለማቀፉ የንግድ ማህበረሰብ ብሔራዊ እና አህጉራዊ የተፈጥሮ አካባቢዎች ጥበቃ እንዲደረግላቸው ይሻል፣ በዋጋ ሰንሰለቱ ላይ በሁሉም ግብዓቶች የንግድ እቃዎች እና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የጥራት ደረጃዎች እና የአካባቢ ጥበቃ ደንቦችን እንዲያሟሉም ይፈለጋል:: ጥብቅ የአካባቢ ጥበቃ እና የአመራር ደረጃዎችን እንደ አንድ የአገሪቱን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ መውጫ ዘዴ እና መቋቋሚያ የብሔራዊ ጥበቃ አካል አሠራር ዝርጋታ እና ትግበራን ለማረጋገጥ መንግስት እርምጃዎችን እንዲወስድ የጥራት ፖሊሲው ያስገድዳል::*

*የጥራት ፖሊሲዉ በንግዱ፣ በሰዎች ደህንነት እና ጤና እንዲሁም በዱር እንስሳት፣በእፅዋትና በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ይኖረዋል:: የጥራት ፖሊሲ የንግድ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች እና የነዚህኑ አካባቢያዊ ትክክለኛነት ጥራትና ደህንነት የሚደግፍ እና የሚያሳድግ ሆኖ እነዚሁ ምርቶችና አገልግሎቶችም በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ተገቢ መስፈርቶችን ለማሟላታቸዉ ተቀባይነት ያለዉ ማስረጃ የሚሰጥ ይሆናል:: የጥራት መሰረተ ልማት ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥና ለማበረታታት እንዲሁም ለአካባቢና ማህበረሰባዊ ደህንነት ወሳኝነት ያለው ነገር ነዉ:: የጥራት ፖሊሲዉ የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ተቋሞች የሚሰጧቸዉ አገልግሎቶች ዜጎች ንፁህ፣ ደህንነቱ በተጠበቀና ጤናማ አካባቢ እንዲኖሩና እንዲሰሩ እንዲሁም የሴቶች፣ የህፃናት እና የአካል ጉዳተኞች መብት ተጠቃሚነት በቂ ሁኔታ የሚደግፍ የሸማቾች ጥበቃን ማጠናከር፤ ዜጎች ጤነኛ*

ምርቶችንና አገልግሎቶችን በቀላሉ እና ባልተቆራረጠ መልኩ ተደራሽ እየሆኑ የሁል ጊዜ ፍላጎታቸውን እያሟሉ ምጣኔ ሃብታዊ፣ አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን ሚዛን ለማረጋገጥ መንግስት የተቀናጀ አካባቢዊና ማህበራዊ ደህንነቶችን ለማበረታት እና ለማጠንከር ቁርጠኝነት አለው፡፡ የጥራት ፖሊሲዉ ተወዳዳሪነትን ለድርድር ሳያስገባ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ደረጃዎችን ለማሟላት የጥራት ፖሊሲው ለምጣኔ ሃብት ዘርፎች የማህበራት ማህበራዊ ኃላፊነቶችን እንደ ስኬታማ መሣሪያ በመውሰድ አፅእኖት ይሰጣል፡፡

የጣልቃ ገብነቱ አግባቦች በሃብቶች አጠቃቀም ውጤታማነት እና ፅዱ አመራረት፣ ዘላቂነት ያለው ፍጆታ እና አመራረት፣ መልሶ የመጠቀም ምጣኔ ሃብት፣ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማትን፣ የአካባቢ አስተዳደር ስርዓት ደረጃዎችን በኃላፊነት ማውጣት፣ የሥራ ደረጃዎች እና የአሠራር ሁኔታዎችን፣ የሠራተኞች እና የማህበረሰቡ መስተጋብርን፣ ማህበራዊ ፍትህዊነትን፣ የስርዓተ-ፆታ መመጣጠንን፣ ሰብአዊ መብቶችን፣ መልካም አስተዳደርን፣ የፀረ- ሙስና እርምጃዎችን፣ የስጋት ግምገማዎችን፣ ተሞክሮዎች መዉሰድን፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከብሔራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለማቀፋዊ ደረጃዎችና ቴክኒካዊ ደንቦች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥን ይጨምራል፡፡

## 6.7 *ባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች*

### 6.7.1 ስርአተ-ጾታ እና ወጣቶች

በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች እና ወጣቶች ከፍተኛ የህብረተሰብ አካል በመሆናቸው በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በህገ መንግስቱ ተቀምጧል። በመሆኑም በተለያዩ ሴክተሮች ፖሊሲዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለሆነም በአገራዊ የጥራት ፖሊሲ ውስጥ ሥርዓተ ፆታና ወጣቶች ለጥራት ባህል እንዲገነባ ትልቅ ትኩረት ሊሰጡና በሀገሪቱ የጥራት መሠረተ ልማትስርአት በማረጋገጥ ረገድ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለባቸው። በሌላ በኩል በተለያዩ የምርትና የአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ ሴቶች እና ወጣቶች የጥራት ደረጃዎችን እንዲያሟሉ አስፈላጊውን ድጋፍ በመንግስት እንዲያገኙ ይደረጋል። እንዲሁም የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟሉ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን የሚያቀርቡትን ደግሞ የማበረታታት ስራ ይሰራል።

### 6.7.2 አካል ጉዳተኞች

አካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ ህብረተሰብ አካል በመሆናቸው በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የተለያዩ ጉዳዮች እንዲሳተፉ፣ ለነሱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና ድጋፍ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ህገ መንግስቱ ተቀምጧል። በመሆኑም በተለያዩ ሴክተሮች ፖሊሲዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በአገራዊ የጥራት ፖሊሲ ውስጥ አካል ጉዳተኞች በደረጃ ዝግጅት፣ የጥራት ባህል ግንባታ ሂደት ትልቅ ትኩረት እንዲሰጡና በሀገሪቱ የጥራት መሠረተ ልማት ስርአት በማረጋገጥ ረገድ በንቃት እንዲሳተፉ ይደረጋል። በሌላ በኩል በተለያዩ የምርትና የአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ አካል ጉዳተኞች የጥራት ደረጃዎችን እንዲያሟሉ አስፈላጊውን ድጋፍ በመንግስት እንዲያገኙ ይደረጋል። እንዲሁም የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟሉ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን የሚያቀርቡትን ደግሞ የማበረታታት ስራ ይሰራል።

## 7. የፖሊሲ ትግበራ መዋቅር

ይህ ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ለዘርፈ ብዙ እድገት ወሳኝ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል። በዚህ ረገድ መንግሥት የተለያዩ የሚመለከታቸው አካላትን አቅም በማቀናጀት የሕዝብንና የግል ዘርፉን ሀብት በማስተባበርና ዉጤታማ በሆነ አግባብ በመጠቀም ፖሊሲውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ስትራቴጂያዊ አመራር ይሰጣል፤ አስፈላጊውን ሕጋዊና ተቋማዊ መዋቅርም ያዘጋጃል።

### *7.1 የሕግ ማዕቀፍ*

የጥራት መሰረተ ልማት መዋቅር እና የቴክኒካዊ ደንብ ማእቀፍ ያለበት አዉድ በአዋጅ የተደገፈ ህጋዊነት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ በተለይም የመንግስት የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት መዋቅር ዓላማቸዉ፣ የተቆጣጣሪ ባለስልጣን መ/ቤቶች፣ አስተዳደርን፣ ፋይናንስን፣ የስራ ሂደትን እና ተግባራትን ለማስተዳደር በአዋጅ የተገደቡ/የታሰሩ ናቸዉ፡፡የጥራት ፖሊሲዉን ትግበራ ለማሳለጥ መንግስት እንደ ቅድሚያ እርምጃ ነባሩን የህግ ማዕቀፍ ለመከለስ ቁርጠኝነት ማሳየት፣ ከሌሎች ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች አንፃር መቃኘት እና በሀገሪቱ ዉስጥ ካሉ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ግዴታዎች ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**የሚከለሱ ነባር የህግ ማዕቀፎች**

የሚከለሱ ነባር ህጎች የሚከተሉትን ህጎች ሊያካትቱ ይገባል ፡፡ ይህ ሲባል ግን እነዚህ ብቻ ናቸዉ ማለት አይደለም፡፡

*ሀ.* ሀገራዊና የአለም ዓቀፍ የቴክኒክ ደንብ ማዕቀፍን የሚያከብር መሆኑን ለማረጋገጥ በማንኛውም ሚኒስቴርና የቁጥጥር ባለስልጣን ተቋማት ውስጥ የጥራት ቁጥጥር አካላትን ማቋቋሚያ እና ሥልጣንን የሚመለከቱ ሕጎች ሁሉ፣

ለ. የብሔራዊ የደረጃዎች ደንብ፤

ሐ. የብሔራዊ አክሪዲቴሽን ደንብ፤

*መ.* የብሄራዊ ስነ ልክ ደንብ፤

*ሠ.* የብሄራዊ የተስማሚነት ምዘና ደንብ፤

**የሚወጡ አዲስ ህጎች**

አዲስ የሚወጡ ህጎች የሚከተሉትን ህጎች ሊያካትቱ ይገባል፡፡ ይህ ሲባል ግን እነዚህ ብቻ ናቸዉ ማለት አይደለም፡፡

*ሀ.* የቴክኒክ ደንብ ማዕቀፍ አዋጅን በማዘጋጀት በሁሉም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና የተቆጣጣሪ ባለስልጣን መ/ቤቶች የሚከናወኑ የቴክኒክ ደንቦች አፈፃፀም ወጥ በሆነ መመሪያ እንዲተገበር ማድረግ፡፡ ይህ አዋጅ በቴክኒክ ደንቦች ውስጥ የሀገሪቱ ደረጃዎችን ፣ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት አቅርቦትን ፤ የአክሪዲቴሽን ቴክኒካል ብቃት መለኪያ ዕውቅናን በመጠቀም የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተቋማት ኃላፊነቶች እና የሚወስዷቸውን ህጋዊ እርምጃዎች በተመለከተ መመሪያ ይሰጣል።

ለ. የብሄራዊ የጥራት ፖሊሲ ካውንስል ማቋቋሚያ አዋጅ፤

ሐ. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መ/ቤቶች እየተተገበሩ የሚገኙትን የቴክኒካዊ ደንብ ማዕቀፎች ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በተቀናጀ መልኩ መተግበራቸውን የማረጋገጥ ስልጣን ያለው የሀገሪቱ ብሄራዊ የቴክኒክ ደንቦች ማስተባበሪያ ቢሮን ማቋቋም፡፡

መ. የክብደቶችን እና የልኬት ተግባራትን ለማከናወን መሰረታዊ የስነ ልክ አዋጅ በማሻሻል የህጋዊ ስነ ልክ አዋጅን ማዉጣት፡፡

ሠ. በዚህ ፖሊሲ በተደነገገው መሰረት የጥራት መሠረተ ልማትን በማቋቋም አሁን ያሉ ተቋማትን መገምገም፣ አዳዲስ መዋቅሮችን ማቋቋምና ኃላፊነት መመደብ የጥራት መሠረተ ልማት አካባቢው ለአገሪቱ ዕድገት የሚፈለገውን አገልግሎት ለመስጠት ምቹ ሁኔታን መፍጠር ይኖርበታል። በሀገሪቱ የተለያዩ የጥራት መሠረተ ልማት ተቋማት መካከል ቁጥጥር፣ መደራረብ እና የጥቅም ግጭት እንዳይኖር የተቀናጀ አካሄድ ያስፈልጋል።

### 7.2 *ተቋማዊ ዝግጅት*

በከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ በመንግስት የሚወከልና በንግድ ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሰብሳቢነት የሚመራው የብሄራዊ የጥራት ምክር ቤት የሀገራዊ የጥራት ፖሊሲዉ ስኬታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበር ስትራቴጂያዊ አመራር እንዲሰጥ ስልጣን ተሰጥቶታል።

ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፖሊሲ ትግበራ ማዕቀፉ አማካኝነት የተቀመጡላቸውን ሚናዎች ይወጣሉ፤በመደበኛ ሁኔታ በሚደረገው የትግበራ ግምገማ በመሳተፍና ለውጡን በተቋማቸው በማስተግበር ለፖሊሲው ተፈጻሚነት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ የጥራት ፖሊሲውን በማስፈጸም ረገድ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸው ኃላፊነትና ተግባር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 7.2.1 *የጥራት መሠረተ ልማት ተቋማት*

የብሔራዊ የጥራት መሠረተ ልማት ተቋማት መዋቅር የደረጃዎች ዝግጅትና ትግበራ፣ የስነ-ልክ (ሳይንሳዊ፣ ኢንዱስትሪያል እና ህጋዊ)፣ የአክሪዲቴሽን እና የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶችን (የኢንስፔክሽን፣ የፍተሻ፣ የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና የካሊብሬሽን አገልግሎቶች) ማቋቋም እና መተግበርን የሚጠይቅ አጠቃላይ የተቋማዊ ማዕቀፍ (የመንግስት ወይም የግል) ሆነው ሊቋቋሙ ይችላሉ።

የጥራት መሰረተ ልማት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለምርቶች እና አገልግሎቶች አቅራቢዎች፣ ለተጠቃሚዎች እና ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መ/ቤቶች አገልግሎት መስጠት መቻል አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት አገልግሎቶች እንደአስፈላጊነቱ በግል ዘርፍ ውስጥ ሊሰሩ እንደሚችሉ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ስር የሚሰሩ የተለያዩ የፍተሻ ላቦራቶሪዎችን ያጠቃልላል።

የኢትዮጵያ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ፣ እንዲሁም የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ወቅታዊ ፍላጎቶችን በሚመጥን መልኩ ሊቋቋሙ ይገባል። ይህ የሚከናወነው የብሔራዊ የደረጃዎች ተቋም፤ የብሔራዊ የስነ፡ልክ ተቋም ፤ የብሄራዊ አክሪዲቴሽን ተቋም እና የተስማሚነት ምዘና ስርዓት ዋና ቅንጅት ነው።

በአለም የንግድ ድርጅት የንግድ ዝውውር ያለገደብ ስምምነት (WTO-TBT) ውስጥ የተገለጹት ቴክኒካዊ ደንቦች የሰዎችን ደህንነት እና ጤና፣ የእፅዋት እና የእንስሳት ጤና፣ የሸማቾች እና የአካባቢ ጥበቃ እንድሁም የፍትሃዊ ንግድ ዝውውርን ይመለከታል፡፡ በአለም የንግድ ድርጅት የንግድ ዝውውር ያለገደብ ስምምነት (WTO-TBT) የቴክኒክ ደንቦች ለንግድ አላስፈላጊ እንቅፋት እንዳይሆኑ ወይም አድሎአዊ ተጽእኖ እንዳይኖራቸው ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

የቴክኒክ ደንቦች ተዘጋጅተው የሚተገበሩት እንደ ግብርና፣ ኮንስትራክሽን፣ ኤሌክትሪክ፣ አካባቢ፣ ጤና፣ ኢንዱስትሪ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ቱሪዝም፣ ንግድ፣ ትራንስፖርት፣ ማዕድን ሀብት እና ሌሎችም ሚኒስትር መ/ቤቶች ባሉ ብቃት ባላቸው አካላት ነው። የቴክኒካዊ ደንብ ቴክኒካዊ እና አስተዳደራዊ ተግባራትን በማዋሃድ የጥራት መሰረተ ልማት ሙሉ የትግበራ መዋቅርን ይሰጣል፡፡የቴክኒክ ደንቦች የአንድ ሀገር የህግ አውጭው ስርዓት አካል ሲሆኑ እንዲተገበሩ በህግ  የተደነገገ ነው፡፡

ሀ. ብሔራዊ የደረጃ ተቋም

በሀገሪቱ ዉስጥ የብሔራዊ የደረጃዎች ዝግጅት ኃላፊነት ያለው አንድ ብሄራዊ የደረጃ ተቋም ብቻ ይኖራል። የደረጃዎች አዘገጃጀት ዓለም አቀፍ የደረጃዎች አዘገጃጀት ስርዓትና እና የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አሠራርን ይከተላል።

ለ. ብሔራዊ የአክሪዲቴሽን ተቋም

መንግሥት የተስማሚነት ምዘና አካላትን ዕውቅና ለመስጠት፤ ለማበረታታት እና ለመደገፍ አንድ ብሔራዊ የአክሪዲቴሽን ተቋም ብቻ ማቋቋም አለበት።

ሐ. ብሔራዊ የሥነ-ልክ ተቋም

የብሔራዊ የሥነ-ልክ ተቋም የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ የጥራት መሠረተ ልማት  አንዱ መዋቅር ነው። የብሔራዊ የስነ-ልክ ተቋም ሁለቱንም የሳይንስ እና የኢንዱስትሪ የስነ-ልክ መስፈርቶችን ይመለከታል፡፡

መ. የተስማሚነት ምዘና ተቋማት

የተስማሚነት ምዘና ማለት የተለያዩ አገልግሎቶች የጋራ መጠሪያ ሲሆን የአንድ አቅራቢ ምርት ወይም አገልግሎት በደረጃዎች ወይም በቴክኒክ ደንብ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ለመሆኑ የሚረጋገጥበትና ማስረጃዎች የሚቀርብበት ሂደት ነው። ፍተሻ፣ ኢንስፔክሽን፣ የፍተሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት(ምርት እና ስርዓት)፣የልኬት ንጽጽር እና መለኪያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ፤ በአጠቃላይ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶች ተደርገው ይወሰዳሉ። በተስማሚነት ምዘና ተቋማት በሁለቱም በግል እና በመንግስት ጥላ ውስጥ የሚሰጡት አገልግሎቶች አግባብነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ የደረጃ መስፈርቶችን የሚያሟሉ እና በዓለም አቀፍ የአክሪዲቴሽን አካል እውቅና የተሰጣቸው ናቸው።

ሠ. የቁጥጥር ባለሥልጣን

የአገሪቱ የቴክኒክ ደንብ ሥርዓት የህግ አወቃቀር እንደ ክልላዊ ንግድ ስምምነቶችን፣ የአለም የንግድ ድርጅት የንግድ ዝውውር ያለገደብ ስምምነት (WTO-TBT) እና SPS (ሳኒቴሽን እና ፋይቶ ሳኒተሪ) የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ፣ ተዛማጅ ሕጎችን

እና ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን ባሟላ መልኩ መገምገም እና ማስተካከል አለበት። ይህም በጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት እና በብሔራዊ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መ/ቤቶች እንዲሁም በክልላዊ እና አለም አቀፍ አቻ ተቋማት ጋር ውጤታማ ትብብር መፍጠርን ያካትታል።

መንግስት ለቴክኒክ ደንቦች አተገባበር ተገቢውን የገበያ ክትትል የሚያደርጉ በቂ አቅም ያላቸው ጠንካራ ተቆጣጣሪ አካላት በአገር አቀፍ ደረጃ በማቋቋም አቅማቸውም በዘላቂነት እንዲገነባ ያደርጋል። ሁሉም ተቆጣጣሪ አካላት በተሰጣቸው ስልጣን ተግባር ወሰን ውስጥ ብቻ የቁጥጥር ስራን እንዲያከናውኑ መንግሥት ያደርጋል።

ረ. ህጋዊ ሥነ-ልክ

አሁን ያሉት የሕጋዊ ሥነ-ልክ ቁጥጥር ሥርዓት ሕጎችን በመገምገምና በማሻሻል ወደ ፊት ከሚዘጋጀው አዲሱ የቴክኒክ ደንብ ጋር በተጣጣመና ወጥ በሆነ መልኩ እንዲተገበር እራሱን የቻለ የሚመለከተው የመንግሥት ኤጀንሲ ሊቋቋም ይችላል። የሕጋዊ የሥነ-ልክ ተቋማት የተሻለ የሕጋዊ ሥነ-ልክ አፈጻጸም እንዲኖራቸውና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ መንግሥት አስፈላጊ ግብዓቶችን (ማለትም የገንዘብ ድጋፍ፣ አቅርቦት፣ተሽከርካሪዎች፣ የመለኪያ መሣሪያዎች ማነጻጸሪያዎችን እና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል) ያቀርባል እንዲሁም በዘርፉ አክሪዴት እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ሰ. ብሔራዊ የጥራት ካውንስል

ብሔራዊ የጥራት ካውንስል ከመንግስት የጥራት መሠረተ ልማት ተቋማት ጋር በመተባበር ለብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ትግበራ ሂደት የማስተባበር ኃላፊነት አለበት። የጥራት መሰረተ ልማት መዋቅር ከዚህ በታች የተገለጹ ተቋማትን ማለትም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ፣ኢንዱስትሪ ፣ ግብርና ፣ ማዕድን ፣ ውሃ ፣ ኢነርጂ ፣ ኮንስትራክሽን ፣ አካባቢ ፣ ትራንስፖርት ፣ ጤና ፣ ትምህርት ፣ ፈጠራ እና ቴክኖሎጂ ፣ ኢኮኖሚ ልማት ፣ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ፣ የወጪ ምርት ልማት ምክር ቤት ፣ ማህበራት (ሙያዊ ፣ ንግድ ፣ ሸማቾች፣ አካዳሚ ፣ ሲቪል ማህበረሰብ)የሚያካትት ቢሆንም በነዚህ ብቻ ላይወሰን ይችላል።

ለካውንስሉ ተግባራዊነትና አስፈላጊነት አጽንዖት ተሰጥቶት በመንግስት በሚወከል ከፍተኛ ኃላፊ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ የካውንስሉ ተግባር በብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ትግበራ መርሃ ግብር ወሰን ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዱን ተግባራትን ከማስተባበር በተጨማሪ የመንግስት መከላከያ እና ደህንነት አካላት ልዩ ባህሪን በማክበር ከኢንዱስትሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማሻሻል ነው ።

ካውንስሉ የጥራት ፖሊሲ ትግበራ እቅድን የመከታተል እና አፈፃፀሙን ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ሀላፊነት አለበት። እያንዳንዱ ሚኒስቴር መ/ቤት እና ኤጀንሲዎች ተለይተው የታወቁትን የብሄራዊ የጥራት ፖሊሲ ክፍልን የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው። ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ ኤጀንሲዎች እና የአካባቢ መስተዳድር ተቋማት ፖሊሲውን ከማስፈጸም አንጻር ከካውንስሉ ጋር በቅርበት ይገናኛሉ።

የሚመለከታቸው ሚኒስትር መ/ቤቶች የብሄራዊ የጥራት ፖሊሲን ከራሳቸው ፖሊሲ ጋር በማቀናጀት ያለምንም ችግር መተግበሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት እና ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መ/ቤቶች መካከል ምንም አይነት የቁጥጥር ስልጣን መደራረብ እና የጥቅም ግጭት እንዳይኖር የተናበበ እና የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ያስፈልጋል።

### 7.2.2 አጋር አካላት ሚና

#### *7.2.2.1 የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ*

መንግስት የብሔራዊ የጥራት ፖሊሲን ተግባራዊ ሲያደርግ ህዝባዊና የግል አጋርነት ዘዴን ያበረታታል እንዲሁም ከግሉ ዘርፍ፣ ልማታዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ፤ የሸማቾች ድርጅቶች እና ሲቪል ማህበራት ውጤታማ የቅንጅትና የትብብር ዘዴዎችን ይዘረጋል፡፡

በተለይም መንግስት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናል፡፡

ሀ. የግሉ ዘርፍ ስራዎቻቸውን በተወዳዳሪነት እንዲሰሩ እና ጥራት ያላቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ለንግድ እንዲጠቀሙ፤ ብሔራዊ ደረጃዎችን እንዲጠቀሙና የጥራት ስራ አመራር ሥርዓትን ስራ ላይ እንዲያውሉ ይደግፋል፣

ለ. በጥራት መስክ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመጠቀም የምርትና አገልግሎቶችን ጥራት በማሻሻል ለኢትዮጵያ ምርቶችና አገልግሎቶች ተወዳዳሪነት አስተዋጾ ማድረግ፣

ሐ. የግሉ ዘርፍ በመዋቅራዊ ውክልና እና በቴክኒካዊ ኮሚቴ ዉስጥ በመወከል በደረጃዎች ዝግጅት ፣ በአክሪዲቴሽን እና በተስማሚነት ምዘና ስራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታታል፤

መ. የብሔራዊ የጥራት ፖሊሲን ተግባራዊ በማድረግ የተሻሻሉ የገበያ ዕድሎችን በመጠቀም፣ የግሉ ዘርፍ የጥራት መሰረተ ልማት መዋቅር ላይ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈሱ ያበረታታል፣

ሠ. ለብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ተግባራዊነት ከመንግስት፣ ከዓለም አቀፍ ልማት አጋሮች እና ከግሉ ዘርፍ ሀብትን በማንቀሳቀስ ገንዘብ ይመድባል፣

#### *7.2.2.2 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች*

የጥራት ፖሊሲዉ ትግበራ ዉጤታማ እንዲሆን በተለይም ጥራትን እና ልህቀትን ለማስፋፋት፣ ማህበራት፣ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ፤ ኢንዱስትሪዎች፣ የመገናኛ ብዙሀን እና የሁሉንም ማህበረሰብ የነቃ ተሳትፎ በፖሊሲው የተገለፁ ዓላማዎችን እዉን ለማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህ በጥራት ፖሊሲዉ የትግበራ ሂደት ዉስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሚመከከታቸዉ አጋሮቻቸዉ ጋር በትብብር የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናዉኑ ይበረታታሉ

ሀ. የትምህርት ጥራት እና የስልጠና ተግባራትን እንዲያስተዋዉቁ እና እንዲሳተፉ፤

ለ. ከጥራት ጋር የተገናኙ መረጃዎችን በማሰራጨት እንዲሳተፉ፤

ሐ. ጥራትና አካባቢን የሚያሻሽሉ ተግባራትን እንዲተገብሩ፤

መ. በደረጃ ዝግጅት፣ በአክሪዲቴሽን እና በጥራት ቴክኒክ ኮሚቴዎች ዉስጥ የሚመለከታቸዉ አካላት እንዲወከሉ ማድረግ፤

ሠ. ለጥራት ፖሊሲዉ መሻሻል እና ትግበራ የተሻሉ መንገዶችን በተመለከተ ሀሳብ ማቅረብ/መስጠት፤

### 7.2.2.3 ሚዲያ

መገናኛ ብዙሀኑ ከደረጃ እና ጥራት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በማሰራጨት እና ምርታማነትን በማሻሻል የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይበረታታል ፤ በዚህም በአገሪቱ ላይ ላለው ውጤት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ ፡፡

### 7.2.2.4 ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች

በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ሁሉም የዓለም አቀፍ አጋር እና ተቀባይ ድርጅቶች የእድገት እና የአቅም ግንባታ መርሀ-ግብሮች (ፕሮግራሞች) ከጥራት መሰረተ ልማት መዋቅር እና ከቴክኒካዊ ቁጥጥር ጋር የተቆራኙ ናቸዉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉትን መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

- የጥራት ፖሊሲዉን ትግበራ መደገፍ፤
- ቅድሚያ ለተሰጣቸዉ ፕሮግራሞች የሌሎች አጋሮችን ድጋፍ ማስተባበር፤
- ከደረጃ ጋር የተገናኙ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገሪቱ ማሸጋገርን መደገፍ፤
- በቂ ለሆነ የጥራትና ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እድገት የእዉቀት እና የመረጃ ሽግግርን መደገፍ፤
- ተገቢነት ባላቸዉ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተሳትፎዎች ዉስጥ ሀገሪቱን መደገፍ፤
- የጥራት ፖሊሲዉን ትግበራ ለሚያቀላጥፉ ለሀገር ውስጥ ስፔሻሊስቶች እና ቴክኒሻኖች ስልጠና መስጠት፤

## 7.3 የጥራት ፖሊሲው ማስፈፀሚያ ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች

ከጥራት ፖሊሲው የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት የሚያስፈልጉት ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች እንዲሁም ፕሮግራሞቹን የሚፈፅሙትን ተቋማት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

| የተቋሙ ስም ንግ/ቀጣ/ትስ/ሚ/ር | | የኢትዮጵያ የጥራት ፖሊሲ ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የሚጠበቅ ውጤት | ፕሮግራም | ንኡስ ፕሮግራም | የሚመለከተው ተቋም |
| 1 | ጥራቱ የተሻሻለ የምርትና አገልግሎት አቅርቦት | 1. የጥራት ማረጋገጥ ትግበራና ክትትል ፕሮግራም | • ለአምራቹና አገልግሎት ሰጭ በደረጃ ዝግጅት እና ትግበራ ተሳትፎ ን/ፕሮግራም<br>• የጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት ንዑስ ፕሮግራም<br>• ለተስማሚነት ምዘና አካላት የላቀ ብቀት ምስክርነትና ክትትል ስራንዑስ ፕሮግራም<br>• በጥናት ላይ የተመሰረተ የተሟላ የካሌብሬሽን አገልግሎትንዑስ ፕሮግራም<br>• የቴክኒክ ደንብ ማስከበር ስራ ንዑስ ፕሮግራም | • ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚ/ር<br>• ደረጃዎች<br>• ተስማሚነት<br>• አክርዲቴሽን<br>• ስነልክ |
| 2 | በዓለማቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እና ተቀባይነት ያላቸው ዘመናዊ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ተገንብተዋል | 2. ዘመናዊ የጥራት መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮግራም | • የጥራት መሰረተ ልማት ማዕከላት ማስፋፊያ ንዑስ ፕሮግራም<br>• ዘመናዊ የላብራቶሪ እና ኢንስፔክሽን መሳሪዎች ማሟላት ንዑስ ፕሮግራም<br>• የኢንፎርማሽን ቴክኖሎጂ እና የአሰራር ስርዓት መገንባት ንዑስ ፕሮግራም | • የደረጃዎች ኢንስቲትዩት<br>• ሥነልክ ኢንስቲትዩት<br>• ተስ/ም/ተቋማት<br>• ኢት/አክሪ/አገልግሎት<br>• ንግ/ቀ/ት/ሚ/ር |
| | | 3. የሰው ሀይል አቅም ግንባታ ፕሮግራም | • የአጭር እና የረጅም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና ንዑስ ፕሮግራም<br>• የአሰራር እና አደረጃጀት ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም | • ንግድና ቀጣናዊ ትስስርሚ/ር<br>• ደረጃዎች<br>• ተስማሚነት<br>• አክርዲቴሽን<br>• ስነልክ<br>• ት/ሚኒስቴር |
| 3 | በምርትና አገልግሎት ጥራት ላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የጥራት ባህል ተሻሽሏል | 4. የጥራ ግንዛቤ ፈጠራ እና የምርትና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ደህንነት ጥበቃ ፕሮግራም | • የጥራት ስራ በስርዓተ ትምህርት ማሻሻልና መተግበር ንዑስ ፕሮግራም<br>• የጥራት ግንዛቤ ፈጠራ ስራ ንዑስ ፕሮግራም<br>• የምርትና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ደህንነት ጥበቃ ስራ ንዑስ ፕሮግራም<br>• የጥራት መሰረተ ልማት ም/ቤቶች እና ፎረም አቅም ግንባታ ንኡስ ፕሮግራም | • ትምህርት ሚኒስቴር<br>• ንግ/ቀ/ጥ/ሚ/ር<br>• ደረጃዎች<br>• ስነ ልክ<br>• ተስማሚነት<br>• አክርዲቴሽን<br>• ግዥ ኤጀንሲ |

| የተቋሙ ስም ንግ/ቀጣ/ትስ/ሚ/ር | | የኢትዮጵያ የጥራት ፖሊሲ ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የሚጠበቅ ውጤት | ፕሮግራም | ንኡስ ፕሮግራም | የሚመለከተው ተቋም |
| 4 | ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት ጥራት አድጓል | 5. ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት ጥራት ድጋፍ ፕሮግራም | | • ኢንዱስትሪ ሚ/ር<br>• ስራና ክህ/ሚ/ር<br>• ንግ/ቀ/ት/ሚ/ር<br>• ደረጃዎች<br>• ስነ ልክ<br>• ተስማሚነት<br>• አክርዲቴሽን<br>• ስራና ክህሎት ሚኒስቴር |
| 5 | ከዓለማቀፍ፣አህጉር አቀፍና ሀገራዊ የጥራት መሰረተ ልማት አካላት ጋር ያለው ቅንጅትና ትብብር አድጓል | 6. የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ቅንጅት፣ ትብብር እና ተሳትፎ ፕሮግራም | • የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ከአቻ እና አለም አቀፍ ተቋማት ተሳትፎ፣ ቅንጅት እና ትብብር ንኡስ ፕሮግራም<br>• የቴክኒክ ደንብ ትግበራ ቅንጅታዊ አሰራር ንኡስ ፕሮግራም<br>• ሀገራዊ የጥራት መሰረተ ልማት አካላት ቅንጅትና ትብብር ንኡስ ፕሮግራም | • የደረጃዎች ኢንስቲትዩት<br>• ሥነልክ ኢንስቲትዩት<br>• ተስ/ም/ተቋማት<br>• ኢ.ት/አክሪ/አገልግሎት<br>• ንግ/ቀ/ት/ሚ/ር |
| 6 | የጥራት የደረጃ መስፈርቶችን ያሟላ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈጻጸም አድጓል | 7. የዘላቂ ልማት ግቦች አፈጻጸም የጥራት መስፈርት ደረጃ ማሟላታቸውን ማጥናት፣መከታተልና መደገፍ ፕሮግራም | • .የአካባቢ የጥራት ደረጃ መስፈርት አፈጻጸም ንኡስ ፕሮግራም<br>• የማህበራዊ ዘርፍ የጥራት ደረጃ መስፈርት አፈጻጸም ንኡስ ፕሮግራም<br>• ኢንደስትሪ ኢኖቬሽን እና መሰረተ ልማት የጥራ ደረጃ መስፈርት አፈጻጸም ንኡስ ፕሮግራም | • ፕላንና ልማት ሚኒስቴር<br>• የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን<br>• የደረጃዎች ኢንስቲትዩት<br>• ሥነልክ ኢንስቲትዩት<br>• ተስ/ም/ተቋማት<br>• ኢ.ት/አክሪ/አገልግሎት<br>• ንግ/ቀ/ት/ሚ/ር<br>• ትምህርት<br>• ጤና<br>• ከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር |

### 7.3.1 ብሄራዊ የጥራት መሰረተ ልማት የፋይናንስ ድጋፍ

የኢትዮጵያ መንግስት አሁን ያለውን የብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት (NQI) ለማልማት፣ ለማሻሻል እና መልሶ ለማዋቀር በገንዘብ የመደገፍ ሃላፊነት አለበት። በተጨማሪም ብሔራዊ የጥራት ምክር ቤት በመንግስት ሴክተር ውስጥ ያሉ የጥራት መሠረተ ልማት ተቋማትን ጨምሮ ለብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ከህዝብ ፣ ከልማት አጋሮች እና ከግሉ ሴክተር ግብዓቶችን ያሰባስባል።

የግሉ ሴክተር ተቋማትና ድርጅቶች በአገር አቀፍ፣ በክልላዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በቴክኒክ ኮሚቴዎች እና መሰል መዋቅሮች ውስጥ በሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ የደረሰ አይደለም። መንግሥት የግል ተቋምን ብሔራዊ የጥራት ተቋም አድርጎ በሚሰይምበት ጊዜ፣ ተቋሙ በአገራዊ የጥራት ፖሊሲ ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ለመወጣት የሚያደርጋቸውን ሥራዎች በገንዘብ ለመደገፍ በመንግሥትና በልዩ ተቋሙ መካከል የተወሰነ የውል ስምምነት ሊኖር ይገባል።

የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት በሚሰጡዋቸው የተስማሚነትና ምዘና አገልግሎቶች ገበያውን በማያዛባ ሁኔታ ከተጠቃሚው በማስከፈል የራሳቸውን ገቢ እንዲሰበስቡ ይደረጋል ፡፡ ተገልጋዩ የሚጠየቀው የገንዘብ መጠን ተቋማቱ ስራዉን ለመስራት የሚያወጡትን ወጭ የሚሸፍን እና የአነስተኛና መካከለኛ ተቋማት የመክፈል አቅምን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

### *7.4 የፖሊሲው ክትትልና ምዘና ስርዓት*

የጥራት ፖሊሲው ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ ለ10 ዓመታት እንዲያገለግል ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም መንግስት በተለየ ሃላፊነት ክትትል ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፖሊሲው በበርካታ ተቋማት የሚተገበር በመሆኑ ለተግባራዊነቱ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ጥረት ወሳኝ ስለሆነ በአተገባበሩ ሀላፊነት ያለባቸው ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ሁሉ የፖሊሲውን ውጤታማነት መከታተልና መመዘን ይኖርባቸዋል፡፡

የፖሊሲው የክትትልና ምዘና ሽፋን በዋናነት ጥቅል መለኪያዎችንና የውጤት አመልካቾችን በመጠቀም የፖሊሲውን ሂደት፣ ለውጥ፣ዕድገትና ውጤት የሚለካ ይሆናል፡፡ ለውጤታማነቱ ደግሞ የፋይናንስና ብቁ የሰው ሃይል አቅርቦት፣ የባለድርሻ አካላት የትብብርና ትስስር ጉድለትና የመሳሰሉት መነሻዎች የመሳሰሉት ታሳቢ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

የመለኪያና ውጤት አመልካቾቹን በዋናነት የፖሊሲውን አፈጻጸም በወቅቱ ለማረምና ለማስተካከል የሚያግዙ ሲሆኑ በተቻለ መጠን መለኪያ ሊዘጋጅለት የሚችል ሆኖ የፋይናንስ አቅምን፣ጊዜንና ተመሳሳይ መስፈርቶችን ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል

### 7.4.1 የአመልካች አይነቶች

የፖሊሲውን ውጤታማነት ለመመዘን በርካታ አማራጮች ያሉ ቢሆንም በዚህ ፖሊሲ ዋናዋና መለኪያ አመልካቾች የሚሆኑት የፖሊሲ ውጤታማነት እና የፖሊሲው አተገባበር አመልካቾች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

**የፖሊሲ ትግበራ አመልካቾች**

የፖሊሲ ትግበራ አመልካቾች በግብዓት አመልካቾች ና በተግባር አመልካቾች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

የግብዓት አመልካቾች ሲባል ይህን የጥራት ፖሊሲ ለመተግበር የተመደበለት እና የወጣበት ሃብት የሚመዘንበት ሲሆን ይህም በገንዘብ፣በመሰረተልማት ግንባታ፣በላብራቶሪና ሳይንሳዊ መሳሪያዎች አቅርቦትና በሰው ሀብት ስልጠናና አቅም ግንባታ ሊሆን ይችላል፡፡

የተግባራት መለኪያ ደግሞ በፖሊሲው አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ/የነበሩ ጥንካሬና ጉድለቶችን ለመመዘንና ለመለካት የሚያስችል ነው፡፡

**የፖሊሲ ውጤት ምዘና**

የፖሊሲ ፋይዳ ምዘና አመልካች

የጥራት ፖሊሲው ፋይዳ በምርትና አገልግሎት ጥራት ላይ የመጣው ለውጥና በአጠቃላይ በሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይ በመመስረት የሃገራችን ምርትና አገልግሎት በአለማቀፍ ገበያ ላይ ባላቸው የጥራት ተቀባይነትና ተወዳዳሪነት፣የጥራት መሰረተልማት አገልግሎት አሰጣጥና፣በሚዘረጋ የጥራት ቁጥጥር ስርዓትና በተመሳሳይ አመልካቾች የሚመዘንበት ነው፡፡

**አካታችነት**

ይህ መለኪያ የጥራት ፖሊሲው ሴቶችን፣ወጣቶችን፣የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞችን እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ጭምር ከማሳተፍ፣አቅም ከማሳደግና ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር የፖሊሲው ውጤታመነት የሚመዘንበት ነው፡፡

**የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ**

የጥራት ፖሊሲው የሀገራችን ምርትና አገልግሎት ጥራት በብሄራዊ፣ በቀጣናዊና በዓለማቀፍ ደረጃ የተዘጋጁ ደረጃዎችን ከማሟላትና የሀገራችንን የዓለምአቀፍ የገበያ ድርሻ መጠን ከማሳደግ አንጻር መመዘን የሚኖርበት ሲሆን ይህ ውጤት በመንግስት፣በግል ተቋማትና በልዩ ልዩ ማህበራትና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ የሚመዘን ይሆናል፡፡

**አሳታፊነት**

የጥራት ፖሊሲው ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳታፊነት ማለትም የመንግስና የግል ተቋማትንና ዓለማቀፍና የሀገር ውስጥ የልማት አጋሮች እንዲሁም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተሳትፎ ሁሉ የሚያረጋግጥ መሆን ያለበት ሲሆን አንድ የፖሊሲው መመዘኛ ይሆናል፡፡

**የአቅም አመላካቾች**

ይህ የጥራት ፖሊሲ አዳዲስ የምርትና አገልግሎት ደረጃ የማውጣት እና የመከለስ፣ የስነልክ እና የአክሪዲቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ እና የተስማሚነት ምዘና እንዲሁም የቁጥጥር ስርዓትን አቅም ከመገንባት አኳያ ምዘናው የሚከናወንበት ነው፡፡

### 7.4.2 የፖሊሲ ክለሳ

ይህ የጥራት ፖሊሲ ቢያንስ ለአስር ዓመታት እንዲያገለግል ታሳቢ የተደረገ ሲሆን በየወቅቱ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የሚመዘን እና የሚገመገም ይሆናል፡፡ይህም ፖሊሲውን ለመከለስ፣ አፈጻጸሙን ለማስተካከልና ለማረም ያስችላል፡፡ በዚህም መሰረት ይህ

የጥራት ፖሊሲ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት፣በሶስት ዓመት፣በአምስት ዓመትና በመጨረሻም የፖሊሲው የማጠቃለያ ዘመን የማጠቃለያ ግምገማ ይደረጋል፡፡

## 8. የፖሊሲው ስርጭት

የፀደቀው የፖሊሲ ሰነድ በህትመት፣በሶፍት ኮፒ እና ሌሎች መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## 9. ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ፖሊሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ከ ……ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ፡፡ ይሆናል፡

## 10. የቃላት ፍች

**"አክሪዲቴሽን"** ማለት የተስማሚነት ምዘና አካላትና የሥራ አመራር ሥርዓት አማካሪዎች አስቀድሞ የተወሰነ የብቃት መስፈርቶችን መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በሚካሄድ ግምገማ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፡፡

**"ካሊብሬሽን"** ማለት በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ በመለኪያ መሣሪያው በመጀመሪያ ደረጃ የተገለፀው የልኬት መጠን፣ የመለኪያ ሥርዓት ወይም የማመሳከሪያ ስርዓት በመለኪያ ከተገለፀው እሴት ጋር ያለውን አንድነት ወይም ልዩነት ለማወቅ የሚደረግ ንጽጽር ነው

**"ሰርተፍኬሽን"** ማለት አንድ ምርት ወይም አገልግሎት ወይም የሥራ አመራር ሥርዓትና ሂደትበተገቢ እና የተፈለገውን የተስማሚነት ምዘና መስፈርት አሟልቶ የቀረበ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ሂደት ነው፡፡

**"የተስማሚነት ምዘና"**ማለት ምርትን፣ አገልግሎትን ወይም የሥራ አመራር ሥርዓትን የሚመለከቱ ደረጃዎችና ሕጋዊ መስፈርቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሂደት ነው፡፡

**"ኢንስፔክሽን"** ማለት የምርት ወይም አገልግሎት ወይም ሂደት ከተቀመጡላቸው መስፈርቶች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚደረግ የዕይታ፣የመለካት ፣የመመዘን እና በቤተ ሙከራ ፍተሻ የማከናወን ተግባር ነው፤ ሙያዊ ግምትን ጨምሮ፤

**"መደበኛ መለኪያ"** ማለት አንድን አሃድ ወይም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የመጠን እሴቶችን ለመወሰን፣ በተግባር ለመግጽ፣ ለመጠበቅ ወይም ለመቅዳት የተመደበ መሠረታዊ መለኪያ፣ የመለኪያ መሣሪያ፣ የማመሳከሪያ ስሪት ወይም የአለካክ ቅንብር ነው

**"የብሄራዊ የጥራት መሰረተ ልማት"** ማለት አጠቃላይ(የመንግስት ወይም የግል) የጥራት ተቋማዊ ማዕቀፍ ሆኖ አስፈላጊ የሆኑ ደረጃዎች፣ስነልክ፣አክሪዲቴሽን እና ተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ስርዓት የሚገነባና የሚተገብር ሲሆን በተቆጣጣሪ ተቋማትና በገበያ ተቀባይነት ላላቸው ምርትና አገልግሎቶች ተፈላጊ መስፈርት እንዲያሟሉ የሚያደርግ የአሰራር ማዕቀፍ ነው

**"የጥራት ስራ አመራር/አስተዳደር"** ማለት የጥራት ስራን በተቀናጀ መንገድ ለመምራትና ለመቆጣጠር የሚዘረጋ አሰራርና ስርዓት ነው

“**ደረጃ**”ማለት ለጋራና ተደጋጋሚ ጥቅም ፣ መሟላት ያለባቸው ህጎች፣አሰራሮች ወይም የምርት ባህሪያትን እና ተዛማጅ ሂደቶችን ወይም የማምረቻ ዘዴዎችን የሚያስቀምጥ  በጋራ መግባባት ላይ ተመሥርቶ የህግ ስልጣን ባለው አካል የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ የአስተሻሸግና የመለያ ምልክት አደራረግ መስፈርቶችን ያጠቃልላል

“**የቴክኒክ ደንቦች**” ማለት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች በተገቢው ሁኔታ መስፈርቶቹን ጠብቀው የቀረቡ መሆናቸውን የሚገልጽና ዝርዝር ሂደታቸውን የያዘ ደረጃዎችን በማጣቀስ የሚጠቀም አስገዳጅ ሰነድ ነው፡፡

“**ፍተሻ**” ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተስማሚነት ምዘና ባህሪያት መሟላት አለመሟላታቸውን ለማረጋገጥ በግልጽ ተለይቶ የተወሰነ የቅደም ተከተል ሥርዓትን ተከትሎ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

“**ማረጋገጥ**”ማለት የመለኪያ መሣሪያው  የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ ሲሆን፣ ፍተሻን፣ ምልክት ማድረግንና የትክክለኛነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትን የሚጨምር ተግባር ነው፤